

# በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ እስብታዎች



ሩሂ ተቋም





መጽሐፍ 1

# በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ እስብታዎች

ሩሂ ተቋም

የተቋሙ ተከታታይ መጻሕፍት፦

ከዚህ በታች ያሉት በሩሂ ተቋም የተዘጋጁ ተከታታዮቹ የመጻሕፍት ርዕሶች ዝርዝር ናቸው። መጻሕፍቱ ወጣቶች እና አዋቂዎች ማኅበረሰባቸውን ለማገልገል የሚያስችላቸውን አቅም ለማዳበር በሚደረግ ስልታዊ ጥረት ውስጥ እንደ ዋና ተከታታይ ትምህርቶች/ኮርሶች ለመጠቀም ዓላም የተዘጋጁ ናቸው። በተጨማሪም የሩሂ ተቋም የባሃኢ ህጻናት ትምህርት አስተማሪዎችን ለማሰልጠን ከሚጠቅም ከተከታታይ መጽሐፍት ውስጥ ከሶስተኛው መጽሐፍ ቅርንጫፍ ሆነው የሚወጡ ሌሎች የትምህርት/ኮርስ ስብስቦችን፣ እንዲሁም ከመጽሐፍ 5 የታዳጊ ወጣት ቡድኖች አነቃቂዎችን ለማፍራት ሌላ ስብስብ እያዘጋጀ ነው። እነዚህም ከሥር በዝርዝሩ ውስጥ ተመልክተዋል። በመስኩ ላይ ያለው ልምድ እየዳበረ በሚሄድ ጊዜ ዝርዝሩ ይለወጥ ይሆናል፣ እንዲሁም በዝግጅት ላይ የሚገኙ የሥርዓተ ትምህርት ክፍሎች ቁጥር በስፋት ተደራሽ መሆን የሚችሉበት ደረጃ ላይ ሲደርሱ አዳዲስ ርዕሶች ሲጨመሩ እንደሚችሉ መገንዘብ አለብን።

| | |
|---|---|
| መጽሐፍ 1 | በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ እስብታዎች |
| መጽሐፍ 2 | ለማገልገል መነሳት |
| መጽሐፍ 3 | የህጻናት ትምህርት ማስተማር፣ 1ኛ ክፍል |
| | የህጻናት ትምህርት ማስተማር፣ 2ኛ ክፍል (ቅርንጫፍ ኮርስ) |
| | የህጻናት ትምህርት ማስተማር፣ 3ኛ ክፍል (ቅርንጫፍ ኮርስ) |
| | የህጻናት ትምህርት ማስተማር፣ 4ኛ ክፍል (ቅርንጫፍ ኮርስ) |
| መጽሐፍ 4 | መንትያ ክስተቶች |
| መጽሐፍ 5 | የታዳጊ ወጣቶችን ኃይሎች ማጎልበት |
| | መነሻ ፍላጎት፡- የመጽሐፍ 5 የመጀመሪያ ቅርንጫፍ ኮርስ |
| | እየሰፋ የሚሄድ ምህዳር፡- የመጽሐፍ 5 ሁለተኛ ቅርንጫፍ ኮርስ |
| መጽሐፍ 6 | እምነቱን ማስተማር |
| መጽሐፍ 7 | በአገልግሎት ጎዳና ላይ አብሮ መጓዝ |
| መጽሐፍ 8 | የባሃኦላህ ቃል-ኪዳን |
| መጽሐፍ 9 | ታሪካዊ አተያይን/ምልከታን ማግኘት |
| መጽሐፍ 10 | ሕይወታማ ማኅበረሰቦችን መገንባት |
| መጽሐፍ 11 | ቁሳዊ ሐብቶች |
| መጽሐፍ 12 | (በሒደት ላይ) |
| መጽሐፍ 13 | በማኅበራዊ ተግባር መሳተፍ |
| መጽሐፍ 14 | (በሒደት ላይ) |

የማባዛት መብት © 1987፣1994፣1999፣2007፣2020 - ሩሂ ተቋም፣ ኮሎምቢያ
ኅትመት *1.1.1 PE በሴብተምበር 1994 የታተመ*
ኅትመት 4.1.2. *PE ሜይ 2020* ሁሉ በሕግ የተጠበቀ ነው።
*ISBN 978-958-59880 -2-6*

ትርጉም - በአዘጋጁ ፈቃድ ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ በኢትዮጵያ ባሃኢዎች ብሔራዊ መንፈሳዊ ጉባዔ የሥልጠና ተቋም የሂደት ደስክ ተተርጉሞና ታርሞ ለአምስተኛ ግዜ፣ 4.1.4 PE ታህሳስ፣ 2021 ታተመ።

- አዲስ አበበ፣ ኢትዮጵያ
ፖ. ሣ. ቁ. 102 አዲስ አበበ

Ruhi Institute
Cali, Colombia
Email: instituto@ruhi.org
Web site: www.ruhi.org

## ማውጫ

ጥቂት ሃሳቦች ለአስጠኚው ……………………………………………………………………...V

የባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎችን መረዳት ……………………………………………………….....1

ጸሎት ……………………………………………………………………………………..15

ሕይወት እና ሞት ………………………………………………………………………..31

# ጥቂት ሃሳቦች ለአስጠኚው

በሩሂ ተቋም የሚሰጠው የዋናው ተከታታይ ኮርሶች አንደኛው መጽሐፍ የሆነው በመንፈሳዊ ሕይወት ላይ እስብታዎች፣ የሚጠናባቸው አካባቢዎች ቁጥር በመላው ዓለም ለዓመታት በማደግ ላይ ይገኛል። በአብዛኛው ሁኔታ መጽሐፉ፤ በየጊዜው በሚገናኙ የጥናት ክበብ አባላት የሚመሠረት፣ ለመጠነሰፊ ጥናት ለተዘጋጀ እንቅስቃሴ ('ካምፔይን') በጋራ የተሰባሰቡ፣ ወይም በትምህርት ቤት በዓላት ወቅት በካምፕ ውስጥ ሊሰባሰቡ በሚችሉ የወዳጆች ቡድን የሚነበብና የሚወያዩበት ነው። ሁኔታው ምንም ዓይነት ቢሆን አንዱ የቡድኑ አባል አስጠኚ ሆኖ ይሰራል። በአስጠኚው እና ሌሎች ተሳታፊዎች መካከል ያለው ግንኙነት የአስተማሪና ተማሪ ዓይነት አይደለም፤ ሁሉም መማርን በመሻት ሒደት ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ። ነገር ግን አስጠኚው ሚና አልባ የውይይት አመቻች ብቻም አይደለም። በተከታታይ ኮርሶች ውስጥ በቂ የሚባል ቁጥር ስልጠና ያጠናቀቀና ኮርሶቹ የሚያበረታቱትን የአግልግሎት ተግባራት ያከናወነ፣ እያንዳንዱ የቡድን አባል የሚጠናውን መጽሐፍ ዓላማ እንዲያሳካ ለመርዳት የሚችል/የምትችል ነው/ናት። እነዚያ የመጽሐፍ 1 አስጠኚ ሆነው የሚንቀሳቀሱት በዚህ መግቢያ ላይ የቀረቡትን ሃሳቦች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቢዳስሱ አጋዥ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ።

በመላው ዓለም ያሉ ተሳታፊዎች ወደዚህ የመጀመሪያ የተቋም ኮርስ የሚመጡት ከተለያየ ዳራዎች ነው። አንዳንዶቹ ቀደም ብለው የባሃኢ ማኅበረሰብ አባል የሆኑና የተቀበሉትን እምነት ለማገልገል አቅማቸውን ለማሳደግ የፈለጉ ናቸው። ሌሎች ኮርሱን የባሃኢ እምነትን እንደ ሃይማኖት ለመመርመር እንደመግቢያቸው ያዩታል። እንዲሁም ሌሎች በባሃኢ አስተሳሰቦች የተማረኩና እራሳቸውን ከማኅበረሰቡ ዓላማዎችና ጥረቶች ጋር ለማስተዋወቅ የሚሹ ናቸው። በተጨማሪም በተለይ እነዚያ በባሃኢ ማኅበረሰብ የሚካሄዱ በአንድ ወይም በሌላ ፕሮግራም አማካይነት፣ ማኅበረሰብ ለማገልገል አቅማቸውን ለማሳደግ የፈለጉ ቁጥራቸው እያደገ የመጣ ወጣቶች፣ ኮርሱን እንደ መንደርደሪያ ይወስዱታል።

ገና ከውጥኑ፣ የሩሂ ተቋም ኮርሶች በማገዝና በሌሎች በመታገዝ እያንዳንዳችን በራሳችን ፍጥነት የምንራመድበት፣ ለሰው ዘር የአገልግሎት ጎዳናን የሚያመላክት እንደሆነ ለእያንዳንዱ ተሳታፊ ግልፅ ሊሆን ይገባል። ይህን ጎዳና መጓዝ ሁለት እጥፍ ዓላማ መከተል ይፈልጋል፦ የራስን መንፈሳዊና አዕምሮአዊ ዕድገት ለመጎናፀፍ እና ለኅብረተሰብ መለወጥ አስተዋጽኦ ለማበርከት። በጎዳናው ላይ ያለ ዕመርታ መረዳትና ዕውቀት፣ መንፈሳዊ ባህርያትና አስመስጋኝ ምግባሮች፣ እንዲሁም የችሎታዎችና ክህሎቶች ማከማቻ የሚፈልጉ የብዙ ችሎታዎች ዕድገት ይጠይቃል። የተቋሙ መጻሕፍት የዕውቀት ምንጮች የሚቀዱት በአንድ ወገን ከባሃኢ እምነት ትምህርቶች፣ በሌላ በኩል የዓለም አቀፍ ባሃኢ ማኅበረሰብ ቁሳዊና መንፈሳዊ ስልጣኔን ሲያራምድ ከተከማቹ ተሞክሮዎች ናቸው። ተቋሙ መነቃቃትን የሚያገኘው መሆን የምንችለው ግለሰብ እና ልንገነባ የምንችለውን ስልጣኔ ከሚያሳየን የባሃኦላህ ራዕይ ነው። ሁሉም ተሳታፊዎች ያለምንም ዳራ/የኋላ ተሞክሮ/፣ በሁሉም መጽሐፍ እያንዳንዱ ክፍል ግልጽ የተደረገውን፣ ይህን ራዕይ ለማቀፍ ነፃ እንደሆኑ ታሳቢ ተደርጓል።

እምነቶችና ርዕዮተ-ዓለም (የፖለቲካ ፅንሰ-ሃሳቦች) ተከታዮች ለማፍራት የቻሉትን ማንኛውንም መንገድ ለመጠቀም ዝግጁ በሆኑበት ዓለም፣ ከእምነቱ ጋር ትውውቅ የሌለው አንድ ሰው ስለ ሩሂ ተቋም ፍላጎቶች ቅን ጥያቄዎች፣ በተለይም "ሃይማኖቴን እንድቀይር እየተጠየኩ ነው?" ወይም "ሃይማኖትን እንድቀላቀል እየተጠየኩ ነው?" ሊኖሩት ይችላሉ:: እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች ለአስጠኚው የተከታታይ ኮርሶችን ዓላማ ከላይ ባሉት አበይት ሃሳቦች ለመግለጽ ዕድል ይሰጡታል:: ባሃኢዎች ወዳጆቻቸው ማኅበረሰቡን እንዲቀላቀሉ መጓጓታቸው ተፈጥሮአዊ ቢሆንም፣ የራሳቸው አስተምህሮ ስብከት ውስጥ ከመግባት እንደሚከለክላቸው፣ አስጠኚው ለማከል ይፈልግ ይሆናል:: በተቋም ኮርሶቹ የተከፈቱት የአገልግሎት ጎዳናን መጓዝ የባሃኦላህን ትምህርቶች ይበልጥ በጥልቅ መረዳት የሚጋብዝ፣ መጻሐፍቱ ቁልጭ ባለ መልኩ ለማስቀመጥ የሚጥሩበት ነው፤ እውቅና መስጠት እና እምነት እያንዳንዱ ግለሰብ በነፃነትና ያለግፊት የሚያሰላስልባቸው ጉዳዮች ናቸው::

ስለዚህ፣ ለሁሉም የተከታታይ መጻሐፍቱ ዋና ማዕከል በሆነው የመረዳት ጥያቄ ነው ይህ አንደኛው መጽሐፍ እንዲጀምር የሚጠበቀው:: ከቅዱሳን ጽሑፎች ማንበብ አንድ ሰው በሕይወት ዘመኑ ብዙ ሺህ ገጾች ከማንበብ ጋር ተመሳሳይ አይደለም፣ እንዲሁም "የባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎችን መረዳት" የሚለው ክፍል፣ ከቅዱሳን ጽሑፎች ምንባቦች በየዕለቱ የማንበብና በትርጉማቸው ላይ የማሰላሰል ልምድ፣ ማለትም ተሳታፊዎች በአገልግሎት ጎዳና ላይ ሲሳተፉ በተሻለ የሚረዳ ልምድ ለመኮትኮት ይሻል:: አስጠኚው አጥኚዎችን በጥናታቸው ለመምራት ለግንዛቤ ሰፋ ያለ ሃሳብ መስጠት አለበት::

የባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎች ጥልቅ መንፈሳዊ እውነቶችን ይዘዋል፣ በወሰን አልባ ትርጉማቸው ግንዛቤያችንን ለማሻሻል ብንጥርም ቁርጥ ያለ መጨረሻ ላይ ፈፅሞ እንደማንደርስ እናውቃለን:: በጠቅላላው አንድን ምንባብ ለመጀመሪያ ጊዜ ስናነበው የቀጥተኛ ትርጉሙን መሠረታዊ ግንዛቤ እናገኛለን፣ እናም የክፍሉ ምዕራፍ 1 ይህንን እንደ መነሻ ነጥብ ይወስደዋል:: ስለሆነም "የዓለም መሻሻል ንጹሕና መልካም በሆኑ ተግባሮች፣ አስመስጋኝና ተገቢ በሆነ ጠባይ ሊደረስበት ይችላል"፣ የሚለውን ጥቅስ ካነበቡ በኂላ፣ ተሳታፊዎች "የዓለም መሻሻል እንዴት ሊደረስበት ይችላል?" ተብለው ይጠየቃሉ:: በጨረፍታ ሲታይ ብዙዎቹ እንደዚህ ዓይነቶቹ ጥያቄዎችና መልመጃዎች በጣም ቀላል ይመስላሉ:: ነገር ግን የዓመታት ተሞክሮ በዚህ መልክ መጀመር የሚለውን የተቋም ውሳኔ አሳማኝ ያደርጉታል:: በምንባብ ውስጥ የሚገኘውን የእውነታ ንብርብሮች ለማግኘት ባለ ጉጉት፣ አዕምሮ ቀጥተኛ ትርጉሙን ቸል ሊል እንደማይገባ ሁላችንም ልናስታውስ ይገባል:: ለዚህ የመጀመሪያ ደረጃ ግንዛቤ ትኩረት መስጠት ለቡድን ምክክር ወሳኝ መሆኑንም ያረጋግጣል፤ ግላዊ አስተያየቶች በመለኮታዊ ጥበብ ብርሃን እንዲፈነጥቅባቸው ሲደረግ በቀላሉ የሚደረስበትን፣ የሃሳብ አንድነትን ያጎለብታል::

እዚህ ጋር ከአገባባቸው ውጭ በነጠላ ቃላት ላይ የተራዘመ ውይይት የአብዛኛውን ምንባቦች ቀጥተኛ ትርጉምን ለመረዳት እንደማይጠቅም ማስተዋል አስፈላጊ ነው:: ያን ካልን፣ አልፎ አልፎ ቡድኑ አንድን ቃል ከመዝገበ ቃላት መመልከት ሊያስፈልገው ይችላል:: ሆኖም ይበልጥ ፍሬያማ የሚሆነው፣ ተሳታፊዎቹ የቃላትን ትርጉሞች ከጠቅላላው ዓረፍተ ነገርና አንቀጽ እንዴት እንደሚያወጡ መማር ነው::

ግንዛቤ ከቀጥተኛ ትርጉም ወሰን ባሻገር እንዲሰፋ፣ ሃሳቦች እንዴት ተጨባጭ መገለጫዎችን እንደሚያገኙ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ጠቃሚ ይሆናሉ:: በዚህ ረገድ የሚጠቀሱት ሁሉም ቀጥተኛ መልመጃዎች ናቸው:: ለምሳሌ፣ በምዕራፊ 2፣ ተሳታፊዎች ባነበቡት ምንባብ መሠረት፣ የተወሰኑ ባህርያት አስመስጋኝ መሆናቸውን እንዲወስኑ ይጠየቃሉ:: በተመሳሳይ፣ መልመጃ በምዕራፍ 4 ውስጥ፣ አምስት መልካም ባሕርያትን እንዲጠቅሱና በቅዱሳን ጽሑፎች ውስጥ "የሰው ሁሉ መልካም ባሕርያት

መሠረት” ተደርጎ ከተገለፀው እውነተኝነት ውጭ እነዚህን ማግኘት ይቻል እንደሆነ እንዲወስኑ ይበረታታሉ፡፡

ዓላማውን ለማሳካት፣ ክፍሉ ስለቀረቡት ምንባቦች አንዳንድ ውጤቶች/እንድምታዎች እንዲያስቡ ተሳታፊዎችን በመፈታተን ወደተሻለ የግንዛቤ ዕምርታ ይጋብዛል፡፡ በምዕራፍ 2 ውስጥ፣ “በዓለም ላይ በጣም ጥቂት መልካም ሰዎች በመኖራቸው የእነርሱ ተግባሮች ምንም ውጤት የላቸውም” የሚለው ዓረፍተ ነገር እውነት ስለመሆኑ እንዲወስኑ ይጠየቃሉ፡፡ እዚህ ላይ ፍላጎቱ አስተያየትን ብቻ ለመስጠት አይደለም፡፡ አስጠኚው ቆም ብሎ ተሳታፊዎችን የመልሶቹን ምክንያት መጠየቅ አለበት፡፡ ዓረፍተ ነገሩ የግድ ሐሰት መሆን አለበት ካለበለዚያ ቡድኑ መድረስ ካለበት መደምደሚያ ከሆነው ከቀደመው ምዕራፍ የመጀመሪያው ጥቅስ ጋር ይቃረናል፡፡ ባሃኢዎች ሃጢኣታቸውን ለሌሎች መናዘዝ ይችሉ እንደሆነ የሚጠይቀው ጥያቄም እንዲሁ ያለው መልመጃ ምሳሌ ነው፡፡ በተጠኑት ማናቸውም ምንባቦች በግልጽ ያልተጠቀሰውን፣ በትምህርቶቹ ውስጥ መናዘዝ ኃጢኣትን እንደማስተሰሪያ መንገድ እንዳይቆጠር የሚከለክለውን፣ “ለጥያቄ ከመጠራትህ በፊት ራስህን በየዕለቱ ተቆጣጠር” የሚለውን ጥቅስ ትርጉም በመፈተሽ ሊደረስበት እንደሚቻል ይጠቁማል፡፡

በክፍሉ ውስጥ ያሉት መልመጃዎች በሚካተቱት ምንባቦች ውስጥ የተሸሸጉትን ዘርፈ-ብዙ ትርጉሞች ለማጠቃለል በምንም ዓይነት መንገድ አይሞክሩም፡፡ እያንዳንዱ አስጠኚ ማጤን ያለበት አንድ ጥያቄ በአንድ በተሰጠ መልመጃ ምን ያህል ውይይት መካሄድ እንዳለበት ነው፡፡ እዚህ ጋር ብዙ የተያያዙ ነገር ግን ውሃ የማይቋጥሩ ፅንሰ-ሃሳቦች ላይ ውይይቶችን ማንዛዛት የመጽሐፉን ውጤታማነት ሊቀንሰው እንደሚችል ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው፡፡ እያንዳንዱ ቡድን አሳማኝ የዕድገት ስልተ—ምት መመሥረት ይኖርበታል፤ ተሳታፊዎች በራሳቸው አማራጮች መሠረት ቀስበቀስ እየተሻሻሉ እንደሆነ የተለየ ስሜት ሊሰማቸው ይገባል፡፡ ሆኖም አስጠኚው የአንዳንድ ምዕራፎች መልመጃዎች በጥልቅ ሳይተነተኑ በፍጥነትና ላይላዩን እንዳይታለፉ ትኩረት ማድረግ አለበት፤ ዝም ብለው መልሶችን በመሙላት በዚህ መልክ የቀጠሉ ቡድኖች፣ ዘላቂ ውጤት ፈፅሞ አላገኙም፡፡

አንድ በጥቂቱ ሊጠቀስ የሚገባው የመጨርሻ ነጥብ፡- እያንዳንዱ የቡድኑ አባል በመጽሐፉ የመማር ሒደት ውስጥ እንዲኮተኮቱ ተሳትፎአቸውን ማረጋገጥ በአስጠኚው ላይ ያርፋል፡፡ ተሳትፎን ለማጫር ማንኛውንም ግለሰብ ግፊት ሳያደርጉ እንዲናገር ማድረግ ብዙውን ጊዜ ፈታኝ ነው፡፡ ገና ከጅምሩ ልንገነዘበው የሚገባው ነገር፣ “ይህ ለእርስዎ ምን ማለት ነው?” ዓይነት ጥያቄዎችን በመጠየቅ ይህ ተግዳሮት እምብዛም የሚቀረፍ አለመሆኑ ነው፡፡ እናም እንደዚህ ዓይነቱ ጥያቄዎች ዕውቀትንና እውነትን ወደ ግላዊ አስተያየት/አመለካከት ደረጃ ዝቅ እንዲሉ ያደርጋሉ፡፡ ከዚያም በቡድኑ አባላት መካከል የሚደረግ ምክክር በዕርግጥ ለላቀ ግንዛቤ ዕድገት የሚሰጥበት ድባብ ለመፍጠር አዳጋች መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ ሁለተኛው ክፍል፣ ልክ እንደ አንደኛው፣ ለመንፈሳዊ ሕይወት ጠቃሚ ልማድ የሆነውን በቋሚነት መጸለይን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በመግቢያው ምዕራፍ “የአገልግሎት ጎዳና” ፅንሰ-ሃሳብ፣ ይህንንም ጎዳና ለመጓዝ በሁለት እጥፍ ዓላማ መሞላት እንዳለብን በመጠቀም ያብራራዋል፡፡ ተሳታፊዎች ወደዚህ ዓላማ ተፈጥሮ ጥልቅ ዕይታ የሚሰጣቸውን፣ በቀጣይ ትምህርቶች/ ኮርሶች የሚብራራ ጭብጥ መነሻ የሆኑ የጥቅሶች ስብስብ ይመረምራሉ፡፡

ከዚህ ጭብጥ ዳራ ባሻገር ክፍሉ የጸሎትን አስፈላጊነት ምርመራውን ይቀጥላል፡፡ በቀዳሚዎቹ አንቀጾች ከተገለፁት ጋር ተመሳሳይ አቀራረብ ይጠቀማል፡፡ ጥያቄዎችና መልመጃዎች ከሚጠኑት ቅዱሳን ጽሑፎች የምንባቦችን ትርጉም ግንዛቤ ለማጎልበት በሚሆን መልኩ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ቡድኑ

በክፍሉ ውስጥ ሲዘልቅ፣ አስጠኚው በቀደሙት ዘመናት ሥር ሰደው የገቡ ሃሳቦችን ትርጉሞችና ልምዶች በመተንተን ጥርጣሬዎችን ማስወገድ ይጠበቅበት ይሆናል፡፡ በአንዳንድ ባህሎች የአምልኮ ስርዓት (ሪቿል) እና ቅርጽ የውስጣዊ ሁኔታን አስፈላጊነት ቀስበቀስ አደብዝዞታል፣ በመሆኑም ምግብ አካልን ለማበልፀግ ወሳኝ ከመሆኑ ባልተናነሰ ሁኔታ ለሰው ነፍስ ጸሎት አስፈላጊ መሆኑን ብዙዎች ችላ ይሉታል፡፡

ስለዚህ፣ ከሁሉም በላይ፣ ክፍሉ በተሳታፊዎች ውስጥ "ከአምላክ ጋር ማውጋት" እና ወደ እርሱ የመቅረብ ፍላጎትን ለመቀስቀስ ይሻል፡፡ ወደ ጸሎት ሁኔታ መግባት፣ ይህንንም ስናደረግ የልቦቻችንና የአዕምሮኣችን ዝንባሌ፣ እንዲሁም ለብቻችንም ሆነ በጋራ፣ በአካባቢያችን ሊፈጠሩ የሚገቡ ሁኔታዎች ምን ማለት እንደሆኑ ከተዳሰሱት ሃሳቦች መካከል ናቸው፡፡ በዕርግጥ፣ በጋራ አምልኮ አማካይነት ስለሚፈጠሩት ኃይሎች አንዳንድ ሃሳቦች ከተሰጡ በኋላ፣ ተሳታፊዎች የጸሎትና አምልኮዎች ስብሰባ ለማስተናገድ እንዲያስቡ ይጠየቃሉ፡፡

የመጽሐፉን ሦስተኛ ክፍል፣ "ሕይወት እና ሞት"፣ ማጥናት የአገልግሎት ጎዳናን ለመጓዝ መሠጠትን እና ለዚህም የተሻለ ጥልቅ ትርጉም ለማጎናፀፍ እንደሚያግዝ ተስፋ ይደረጋል፡፡ በዚህ ዓለም ውስጥ የሚደረግ አገልግሎትን በተሻለ የምንረዳው፣ ከምድራዊ ህይወታችን ባሻገር በሚዘልቀው እና ለዘለዓለም በሚቀጥለው የሕይወት የተሟላ ገፅታ ውስጥ ነው ምክንያቱም ነፍሳችን በአምላክ ዓለማት ሁሉ ውስጥ ለዘለዓለም ታድጋለችና፡፡ ከቴክኒካዊ ስልጠና በተለየ፣ በትምህርት ሒደት ውስጥ ተሳታፊዎች ስለሚያደርጉት ነገር ትርጉምና ጠቀሜታ ይበልጥ ንቁ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ተሞክሮ እንደሚያሳየው እራሳቸውን የገዛ ራሳቸው መማር ንቁ፣ ኃላፊነት የሚሰማው "ባለቤት" ሆነው ማየት የሚችሉት እንዲህ ያለው ንቃተ-ህሊና ካደገ ብቻ ነው፡፡

የክፍሉ እያንዳንዱ ምዕራፍ ከባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎች ከአንድ እስከ ሦስት ጥቅሶች፣ በጥቂት መልመጃዎች በማስከተል ይጀምራል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱት ምንባቦች ቋንቋ ከቀደሙት ከሁለቱ የበለጠ ፈታኝ ነው፡፡ በዕርግጥ ቡድኑ በከባድ ቃላት ላይ ብዙ ጊዜ መውሰዱ አስፈላጊ አይደለም፤ አስጠኚው በእያንዳንዱ ምዕራፍ መልመጃዎቹ በትክክል ለማምጣት እየሞከሩ ያሉትን፣ የቀረበውን አንኳር ሃሳብ እያንዳንዱ መጨበጡን ማረጋገጥ ይፈልጋል፡፡

በቀረበው ርዕስ ሁኔታ/ተፈጥሮ፣ ተጨባጭ ምሳሌዎችን ያካተቱ መልመጃዎች ጥቂትና አለፍ አለፍ ያሉ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ በፅንሰ-ሃሳብ ደረጃ የሚገለፁ ናቸው፡፡ በመልመጃዎቹ የተነሱት አንዳንድ ጥያቄዎች በአፋጣኝ ወይም ቁርጥ ባለ መንገድ ሊመለሱ እንደማይችሉ ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡ የተካተቱት ስለ ርዕሱ ግንዛቤን ከፍ ለማድረግ ነው፤ ተሳታፊዎች እንደዚህ ስላሉት ጥያቄዎች ካሰቡ ብቻ፣ የመማር ዓላማው ተሟልቷል ማለት ነው፡፡

የመጀመሪያዎቹ በዛ ያሉ ምዕራፎች በዚህ ምድራዊ መኖሪያ ውስጥ የሰው ልጅን በጋራ በሚመሠርቱት፣ በነፍስ እና በሰው አካል መካከል ስላለ ግንኙነት ያተኩራሉ፡፡ በእነዚህ ምዕራፎች የቀረቡት አንኳር ሃሳቦች ነፍስ ቁሳዊ አካል እንዳልሆነች ነው፤ ከሰው አካል ጋር ያላት ግንኙነት በመስታወት ውስጥ ከሚታይ ብርሃን ጋር ሊመሳሰል ይችላል፡፡ የመስታወቱ በአቧራ መሸፈንም ሆነ የኋላኋላ መሠበር የብርሃኑን ፀዳል ሊያውከው አይችልም፡፡ ሞት የሁኔታ መለወጥ ነው፣ በሰው አካልና በነፍስ መካከል ያለው ቁርኝት ሲቋረጥ፤ ከዚያ በኋላ ነፍስ ወደ ፈጣሪዋ ለዘለዓለም ታድጋለች፡፡

በመቀጠል ክፍሉ ወደ ሕይወት ዓላማ ጥያቄ ያተኩራል — አምላክን ማወቅ እና የእርሱን ቅርበት መቀዳጀት፡፡ እዚህ ጋ ውይይቱ በሁለት ሰፋፊ ጭብጦች ዙሪያ ያጠነጥናል፡፡ አንደኛው በዚህ

ዓለም ላይ የሕይወታችን ዓላማ ሲሆን፣ ሁለተኛው ከሞት በኋላ የነፍስ ጉዞ ነው። ነፍስ የአምላክ ምልክት ናት፤ በመሆኑም ሁሉንም የእርሱን ስሞችና ባሕርያት ልታንፀባርቅ ትችላለች። ሆኖም በሰው ልጅ ውስጥ የመገለፅ አቅሙ ድብቅ/የተሸሸገ ነው፤ የሰው ዘርን ከጊዜ ወደ ጊዜ ለመምራት በሚመጡት በእነዚያ የተቀደሱ ስብዕናዎች፣ በአምላክ ግልፀቶች ዕርዳታ ብቻ ሊጎለብት ይችላል። እነርሱ በሚሰጡት መንፈሳዊ ትምህርት አማካይነት በውስጣችን የተሸሸጉት ሀብቶች ሊገለፁ ይችላሉ።

ከሞት በኋላ የነፍስን ጉዞ በተመለከተ፣ ተሳታፊዎች እንዲያሰላስሉበት ተያያዥ ሃሳቦች ተቀምጠዋል፡- እነዚያ ለአምላክ ታማኝ የሆኑት እውነተኛ ደስታን ይቀዳጃሉ፤ ማናችንም የራሳችንን መጨረሻ ማወቅ አንችልም፣ ስለዚህ እርስበርስ ይቅር መባባል እና ከሌሎች የመሻል ስሜት እንዳይሰማን ማድረግ ይገባል፤ ልክ እንደዚህኛው በቀጣዩም ዓለም፣ ነፍስ ማደጓን ትቀጥላለች እንዲሁም እዚህ ያሳደግናቸውን መንፈሳዊ ችሎታዎች እዚያም ያግዙናል፤ በዚያኛው ግዛት የምንወዳቸውን እናገኛቸዋለን፣ በዚህ ዓለም የነበረንን ሕይወታችንን እናስታውሳለን፣ ከቅዱሳንና የተባረኩ ነፍሳት ጋር ወዳጅነትን እንቀዳጃለን።

ክፍሉ ስለቀጣዩ ዓለም ጥቅሞች ዕርግጠኞች የምንሆንበት እና የዚህ ሕይወት ለውጦችና አጋጣሚዎች እንዳያሳዝኑን በምንጠየቅበት የባሃኦላህ ጽሑፎች ምንባብ ይገባደዳል። ከዚያም ተሳታፊዎች ባጠኑት ላይ በመመርኮዝ ምን እንድምታዎች እንዳለው ለገዛ ራሳቸው ሕይወት እንዲያሰላስሉ ይጠየቃሉ።



# የባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎችን መረዳት

ዓላማ

በየዕለቱ ከቅዱሳን ጽሑፎች ምንባቦችን የማንበብና በትርጉማቸው ላይ የማሰላሰል ልምድ ለማጎልበት

## ምዕራፍ 1

የዚህ ክፍል ዓላማ በየዕለቱ ከቅዱሳን ጽሑፎች ምንባቦችን የማንበብ እና በትርጉማቸው ላይ የማሰላሰል ልማድ እንዲያሳድጉና እንዲያጠናክሩ እርሶን ለማገዝ ነው። ክፍሉ ከቅዱሳን ጽሑፎች ባለ አንድ ዓረፍተ ነገር ጥቅስ እንዲያነቡ በሚጠይቆት ቀላል መልመጃ ይጀምራል፣ ከዚያ ለጥያቄው ጥቅሱ ራሱ መልስ የሆነውን ምላሽ ይሰጣሉ። ለማከናወን ቢቀልም፣ መልመጃው በተገለፁት ጥቅሶች ትርጉም ላይ ለማሰላሰል እና በቃል እንዲያጥኑዋቸው ይረዳዎታል።

**"የዓለም መሻሻል ንጹሕና መልካም በሆኑ ተግባሮች፣ አስመስጋኝና ተገቢ በሆነ ጠባይ ሊደረስበት ይችላል።"[1]**

1. የዓለም መሻሻል እንዴት ሊደረስበት ይችላል? ____________________

**"የባሃ ሕዝቦች ሆይ! በእነዚያ ቃሎቻቸው ከተግባሮቻቸው በሚለዩት ሰዎች መንገዶች እንዳትጓዙ ተጠንቀቁ።"[2]**

2. መጓዝ የማይገባን በነማን መንገዶች ነው? ____________________

**"የሕያው ልጅ ሆይ! ለጥያቄ ከመጠራትህ በፊት ራስህን በየዕለቱ ተቆጣጠር..."[3]**

3. ለጥያቄ ከመጠራታችን በፊት ምን ማድረግ ይገባናል? ____________________

**"በሉ፦ ወንድሞች ሆይ! ጌጣችሁ ተግባራት እንጂ ቃላት አይሁኑ።"[4]**

4. እውነተኛ ጌጣችን ምን መሆን ይገባዋል? ____________________

**"ቅዱሳን ቃላት፣ ንጹሕና መልካም ተግባሮች ወደ ቅድስና ክብር መንግሥት ሰማይ ያርጋሉ።"[5]**

5. ቅዱሳን ቃላት፤ ንጹሕና መልካም ተግባሮች ምን ያደርጋሉ? ____________________

## ምዕራፍ 2

ከዚህ በታች ያሉት መልመጃዎች አሁን ካነበቧቸው ጥቅሶች ጋር የተያያዙ ናቸው። በቡድናችሁ ውስጥ ስለ ምንባቦቹ ጠቀሜታ ላይ ይበልጥ ለማሰላሰል እንዲረዳዎት የታሰበባቸው ናቸው በመሆኑም በዘፈቀደ ሊሠሩ አይገባም። ይህ ማለት እያንዳንዱ መልመጃ በዛ ያለ ውይይት ይፈልጋል ማለት አይደለም። ሆኖም መልመጃው ተገዳዳሪ ሲሆን፣ የቡድናችሁ አስጠኚ በጥልቀት እንድትፈትሹት ያግዙዋችኋል።

1. አንድ ነገር "የሚያስመሰግን" ነው ሲባል፣ ውዳሴ የሚገባው ማለት ነው። ከሚከተሉት የትኞቹ የሚያስመሰግኑ ናቸው?

   ________ ጥሩ ሠራተኛ መሆን
   ________ ሌሎችን ማክበር
   ________ ማስተዋል
   ________ ውሽታም መሆን
   ________ ሰነፍ መሆን
   ________ ሌሎችን ማገልገል

2. "ለጥያቄ ከመጠራትህ በፊት" የሚለው ሐርግ ምን ማለት ነው? ________________________

   ________________________________________________________________

   ________________________________________________________________

3. ከተከታዮቹ ዓረፍተ ነገሮች የትኞቹ እውነት ናቸው?

   ________ በዓለም ላይ በጣም ጥቂት መልካም ሰዎች በመኖራቸው የእነርሱ ተግባሮች ምንም ውጤት የላቸውም።

   ________ አንድ ነገር ከሌሎች ሰዎች አስተሳሰቦች ጋር ስምም ከሆነ ትክክል ነው።

   ________ አንድ ነገር ከአምላክ ትምህርቶች ጋር ስምም ከሆነ ትክክል ነው።

4. ከሚከተሉት የትኞቹ ንጹህና መልካም ተግባራት ናቸው?

   ________ ሕጻናትን መንከባከብና ማስተማር
   ________ ሥርቆት
   ________ ለሌሎች ዕድገት መጸለይ
   ________ ከችግር ለመውጣት ትንሽ ውሸት መናገር
   ________ ሌሎችን መርዳትና ወሮታን መጠበቅ

5. ከተከታዮቹ ሁኔታዎች በየትኞቹ ውስጥ የሰው ቃላት ከእርሱ ወይም ከእርሷ ተግባሮች ይለያል?

   ________ አንድ ሰው ሁላችንም አንድ መሆን እንደሚገባን ደጋግሞ ይናገራል ነገርግን ግጭትን

በሚፈጥር መልኩ ይንቀሳቀሳል።

________ አንድ ሰው የቅድስና ሕይወትን ያወድሳል ነገርግን ከጋብቻ ውጭ ወሲባዊ ግንኙነት አለው።

________ አንድ ሰው መጠጣትን የሚከለክል የሃይማኖት እምነት እንደሚከተል እያወጀ፣ አልፎ አልፎ አልኮል ይጠጣል።

________ አንድ ሰው የወንዶችንና ሴቶችን ዕኩልነት በይፋ ይደግፋል፣ ነገርግን እንደቀጣሪ ለተመሳሳይ ሥራ ለሴቶች ከወንዶች ያነሰ ይከፍላል።

6. አንድ ባሃኢ ኃጢኣቱን ለሌላ ሰው መናዘዝ ይፈቀድለታልን? ______________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

7. ኃጢኣትን በመናዘዝ ፈንታ እርሱ ወይም እርሷ ምን ማድረግ ይገባቸዋል? __________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

8. “የቅድስና ክብር መንግሥተ ሰማይ” የሚለው ሐረግ ምን ማለት ነው? ____________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

9. መጥፎ ተግባሮች በዓለም ላይ ምን ውጤት አላቸው? __________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

10. መጥፎ ተግባሮች በእነዚያ በሚፈጽሚቸው ሰዎች ላይ ምን ውጤት አላቸው? ______________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 3

አሁን ተከታዮቹን ከቅዱሳን ጽሑፎች የተውጣጡ ጥቅሶች አንብቡና አሰላስሉባቸው። ከዚያ በቃላችሁ ለመያዝ/ ለማጥናት ሞክሩ።

**“እውነተኝነት የሰው መልካም ምግባራት ሁሉ መሠረት ነው።”[6]**

1. የሰው መልካም ምግባራት ሁሉ መሠረት ምንድን ነው? ________________________________

“ያለእውነተኝነት ለማንኛውም ነፍስ በሁሉም የአምላክ ዓለማት፣ ዕድገትና ስኬት የማይቻሉ ናቸው::”[7]

2. ያለእውነተኝነት የማይቻል ምንድን ነው? ____________________

____________________

“ሕዝቦች ሆይ! አንደበቶቻችሁን በእውነተኝነት አስውቧቸው፣ ነፍሶቻችሁን በታማኝነት ጌጥ አስጊጧቸው::”[8]

3. አንደበቶቻችንን በምን ማስዋብ ይገባናል? ____________________

____________________

4. ነፍሶቻችንን በምን ማስጌጥ ይገባናል? ____________________

____________________

“ዓይናችሁ ጉድፍ አልባ፣ እጃችሁ ታማኝ፣ አንደበታችሁ እውነተኛ፣ እንዲሁም ልባችሁ የበራ ይሁን::”[9]

5. ዓይናችን እንዴት መሆን ይገባዋል? __________ እጃችንስ? __________
አንደበታችንስ? __________ ልባችንስ? __________

“እነዚያ በአምላክ ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚኖሩት፣ በዘለዓለማዊ ክብር ወንበሮች ላይም የተቀመጡት፣ በረሃብ ቢሞቱም እንኳ፣ ጎረቤታቸው ምንም ያህል ክፉና ዋጋ ቢስ ቢሆንም፣ የጎረቤታቸውን ንብረት እጃቸውን ዘርግተው በሕገ—ወጥነት ሊወስዱ አይፈቅዱም::”[10]

6. በረሃብ ብንሞትም እንኳ ለማድረግ የማንፈቅደው ምንድን ነው? ____________________

____________________

____________________

## ምዕራፍ 4

በምዕራፍ 2 እንዳስተዋላችሁት፣ በዚህ ክፍል ውስጥ አንዳንድ መልመጃዎች ቀጥተኛ መልሶችን ይጋብዛሉ:: እንዲህ ባለ ሁኔታ ስለ መልሱ ጥርጣሬ ካለ፣ የቡድናችሁ አስጠኚ እርስዎ እና አብሮዎት ያሉ ተሳታፊዎች የሃሳብ አንድነት ላይ እንድትደርሱ ሊያግዝዎት ይችላሉ:: ለሌሎች መልመጃዎች፣ ዋጋ ያለው ውይይቱ ራሱ ነው፣ በመሆኑም አንድ ወጥ መልስ አይጠበቅም:: በሚከተሉት ውስጥ፣ መልመጃ 3 የመጀመሪያው ዓይነት ሲሆን፣ መልመጃ 6 በሁለተኛው ምድብ ውስጥ ያርፋል::

1. እውነተኝነት የሰው መልካም ምግባራት ሁሉ መሠረት ነው:: አምስት መልካም ምግባራትን ይዘርዝሩ:- ______________________________

______________________________

______________________________

2. እነዚህን መልካም ምግባራት ያለ እውነተኝነት ልናገኛቸው እንችላለን? ______________

3. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች የትኞቹ እውነት ናቸው?

_______ ምንም እንኳ ውሸት ቢናገርም አንድ ሰው ፍትኸኛ ሊሆን ይችላል::
_______ አንድ የሚሰርቅ ሰው ታማኝ እጅ አለው::
_______ ታማኝ እጅ የእርሱ ያልሆነውን ፈጽሞ አይነካም::
_______ የልቅ ወሲብ ቁሳቁስ መመልከት ጉድፍ አልባ የሆነ ዓይን እንዲኖረን ከሚነግረን የባሃኦላህ ምክር ጋር ተፃራሪ ነው::
_______ እውነተኝነት ማለት አለመዋሸት ነው::
_______ ታማኝነት የነፍስ ጌጥ ነው::
_______ እውነተኛ ያልሆነ አንድ ሰው በመንፈስ ሊያድግ ይችላል::
_______ አልፎ አልፎ ውሸት መናገር ምንም አይደለም::
_______ አንድ ሰው ከተራበ ቢሰርቅም በአምለክ ዘንድ ተቀባይነት አለው::
_______ በኋላ እንመልሳለን ብለን በማሰብ፣ ያለባለቤቱ ፈቃድ አንድ ነገር መውሰድ ስርቆት አይደለም::
_______ በታማኝነት ስንቀሳቀስ፣ ሚዛናዊ እና እውነተኛ ስንሆን፣ ልባችን የበራ ይሆናል::
_______ ያለ ትንሽ ማጭበርበር አንድን ንግድ ውጤታማ ማድረግ አይቻልም::

4. እራስን መዋሸት ይቻላልን?______________________________

5. ውሸት በምንናገርበት ጊዜ ምን እናጣለን? ______________________

6. ሁላችንም እውነተኛና ታማኝ ብንሆን ዓለም ምን ትመስል ነበር? ______________

______________________________

______________________________

______________________________

## ምዕራፍ 5

ተከታዮቹን ጥቅሶች ያንብቡ፤ከዚያም በቃል ለመያዝ ይሞክሩ:: ከቅዱሳን ጽሑፎች ጥቅሶችን በቃል መያዝ በጣም አስመስጋኝ/ አስደሳች ነው፣ በመሆኑም ይህን ለማድረግ የተቻለዎትን ያህል ጥረት ማድረግ ይገባል:: በዕርግጥ ሁሉም ሰው ምንባቦችን በቀላሉ በቃል ለመያዝ አይችልም:: ሆኖም ጥረት

ማድረጉ፣ ሃሳቦቹን በልባችንና በአዕምሮአችን ለመቅርጽ እና በተቻለ መጠን ለዋናው ጽሑፍ በቀረቡ ሃሳቦች ለመግለጽ ይረዳናል።

**"መልካም አንደበት የሰዎችን ልቦች የሚስብ ማግኔት ነው። ይህ የመንፈስ ምግብ ነው፣ ቃላትንም ትርጉም ያጎናጽፋቸዋል፤ የጥበብና የመረዳት ብርሃን ምንጭ ነው።"[11]**

1. መልካም አንደበት እንዴት ተደርጎ ሊገልጽ ይችላል? ______________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

2. መልካም አንደበት በቃላት ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ምንድን ነው? ______________________

______________________________________________________________________

**"እናንት የጌታ ተወዳጆች ሆይ! በዚህ በተቀደሰ ግልጸት ዘመን፣ ግጭት እና ጭቅጭቅ በምንም ዓይነት አይፈቀዱም። እያንዳንዱ ጠብ ጫሪ ከአምላክ ፀጋ ራሱን ይነፍጋል።"[12]**

3. ከላይ ባለው ጥቅስ መሠረት፣ በዚህ ግልጸት ዘምን የማይፈቀደው ምንድነው? ______________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

4. ጠብ ጫሪ ራሱን ምን ያደርጋል? ______________________________________________

______________________________________________________________________

**"በዚህ ቀን በአምላክ ተወዳጆች መካከል እንደ አለመግባባት እና ውዝግብ፣ እንደጭቅጭቅ፣ እንደመቃቃር እና እንደመጨካከን ከመሳሰሉት የበለጠ በዚህ እምነት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ምንም ነገር የለም።"[13]**

5. በአምላክ እምነት ላይ ምን ሁኔታዎች እጅግ ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ? ___________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**"ወዳጅነትን በቃላት ብቻ በመግለጽ አትርኩ፣ በመንገዳችሁ ላይ ለሚያጋጥሟችሁ ሁሉ ልባችሁ በፍቅራዊ ደግነት ይንደድ።"[14]**

6. ምን ዓይነት ወዳጅነት ነው ሊያረካን የማይገባው? ____________________________

______________________________________________________________________

7. በልባችን ውስጥ በድምቀት መንደድ የሚገባው ምንድነው? ______________________________

______________________________________________________________________________

**"የጦርነት ሃሳብ ሲመጣ፣ ይበልጥ ጠንካራ በሆነው የሠላም ሃሳብ ተቃወሙት። የጥላቻ ሃሳብ ይበልጥ ኃይለኛ በሆነ የፍቅር ሃሳብ መደምሰስ አለበት።"**[15]

8. የጦርነትን ሃሳብ መቃወም የሚኖርበት በምንድን ነው? ______________________________

______________________________________________________________________________

9. የጥላቻ ሃሳብ መደምሰስ የሚኖርበት በምንድን ነው? ______________________________

______________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 6

የላይኛውን ጥቅስ ታሳቢ በማድረግ፣ ተከታዮቹን መልመጃዎች ሥሩ።

1. "ማግኔት" ብረትን የሚስብ መግነጢስ ሌላ ቃል ነው። መልካም አንደበት እንደ ማግኔት ሊያገለግል የሚችለው በምን መንገድ ነው?______________________________

______________________________________________________________________________

2. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች የትኞቹ ከመልካም አንደበት ይገኛሉ?

________ "አታስቸግረኝ!"
________ "ይህ ለምን አይገባህም?"
________ "እባክህ፣ ብትቆይ ቅር ይልሃል?"
________ "እንዴት ያሉ መጥፎ ልጆች ናቸው!"
________ "አመሰግናለሁ፣ በጣም ደግ ነህ።"
________ "አሁን ለአንተ ምንም ጊዜ የለኝም፣ ሥራ በዝቶብኛል።"

3. ከሚከተሉት ሁኔታዎች በየትኞቹ ውስጥ ግጭት እና ጭቅጭቅ ይገኛሉ?

________ ሁለት ሰዎች በአንድ ርዕስ ላይ በሚመካከሩበት ጊዜ የተለያየ ሃሳቦችን ይገልፃሉ።

________ በምክክር ጊዜ ሁለት ሰዎች እርስ በርስ ይቆጣጣሉ እንዲሁም ይከራከራሉ።

________ ሁለት ሰዎች እርስበርስ ስለማይነጋገሩ ሳምንታዊ ፀሎተ ሱታፌ ስብሰባ መሳተፍ አቁመዋል።

________ በአንድ ፕሮጀክት ላይ የሚተባበሩ የቡድን አባላት አንዳቸው ሌላቸውን የድርሻቸውን እየተወጡ አይደለም በማለት ያማርራሉ።

4. ከሚከተሉት ሁኔታዎች የትኞቹ የመቃቃር ምልክቶች ያሳያሉ?

________ ሁለት ወዳጆች በመንገድ ላይ ሲተላለፉ እርስ በርስ ችላ ይባባላሉ።

________ ወደ ጸሎተ ሱታፌ ስብሰባ ስትመጣ፣ ሁሉም ሞቅ ያለ ሠላምታ ይሰጡዋታል።

________ አንዳቸው ለሌላቸው ትሁት ቢሆኑም፣ ሁለት የቡድን አባላት በፕሮጀክት ውስጥ በጋራ ለመሳተፍ ፈቃደኛ አይደሉም።

5. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች እውነት መሆናቸውን ይወስኑ፡-

________ አንድ ሰው ስለሌሎች የሚሰማውን በትክክል መናገር ይገባዋል፤ ልባቸው ቢከፋም ምንም አይደለም።

________ ግጭትን ለማስወግድ ሲባል ውሸት መናገር ምንም አይደለም።

________ ጠብን በፍቅር እና ደግነት ማሸነፍ ይቻላል።

________ ቃላት በፍቅር ሲነገሩ ይበልጥ ውጤታማ ናቸው።

________ አንድ ሰው ጥል ከጀመረ ከእርሱ ጋር መጣላት ትክክል ነው።

________ አንድ ሰው ሲታመም ወይም ሲያዝን ቁጡ የመሆን መብት አለው።

________ ስህተት ሲሰሩ በሌሎች ላይ መሳቅ ደግነት አይደለም።

________ በወዳጆች መካከል መኮራረፍ ሲኖር፣ አንዱ ሌላውን ለመቅረብ እያንዳንዳቸው የተለየ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል።

________ በወዳጆች መካከል መኮራረፍ ሲኖር፣ አንዱ ለመቅረብ ጥረት እስከሚያደርግ ድረስ ሌላው መጠበቅ ይገባዋል።

## ምዕራፍ 7

ከሥር ያሉትን ጥቅሶች ያጥኑና በቃልዎ ይያዙ።

**"... ሐሜት የልብን ብርሃን ያጨልማል፣ የነፍስንም ሕይወት ያጠፋል።"[16]**

**"አንተ ራስህ ኃጢአተኛ ስለሆንክ የሌሎችን ኃጢአት አታውሳ።"[17]**

**"እርኩስ ነገር አትናገር፣ በአንተ ላይ ሲነገር እንዳትሰማ፣ የሌሎችንም ጉድለት አታጉላ፣ የራስህ አይሎ እንዳይታይብህ። ..."[18]**

**"የሕያው ልጅ ሆይ! እንዴት የራስህን ጉድለቶች ዘንግተህ በሌሎች ጉድለቶች ላይ ታተኩራለህ?"[19]**

1. ሐሜት በሐሜተኛው ላይ ምን ውጤት አለው? ________________________________

________________________________________________

2. የሌሎችን ኃጢኣቶች ከማውሳታችን በፊት ምን ማስታወስ ይገባናል? ____________________

________________________________________________

3. የሌሎችን ጉድለት ስናጎላ በእኛ ላይ ምን ይደርስብናል? ________________________

________________________________________________

4. ስለሌሎች ሰዎች ጉድለቶች ስናስብ ምን ማስታወስ ይገባናል? ______________________________

_______________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 8

የላይኛውን ጥቅስ ታሳቢ በማድረግ፣ ተከታዮቹን መልመጃዎች ሥሩ፦

1. በሌሎች ሰዎች ጉድለቶች ላይ የሚያተኩር ሰው በነፍሱ ዕድገት ላይ ምን ይፈጠራል? _________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

2. ሐሜት በአንድ ማኅበረሰብ ምን ውጤት አለው? ________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

3. አንድ ወዳጅ ስለሌላ ሰው ጉድለቶች መናገር ሲጀምር ምን ያደርጋሉ? _______________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

4. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች እውነት መሆናቸውን ይወስኑ፦

________ ስለአንድ ሰው ትክክለኛ ጉድለቶች ስንናገር፣ አያማን አይደለም።

________ ስለአንድ ሰው አስመስጋኝ ባሕርያትና ጉድለቶቹ በአንዴ ስንናገር፣ አያማን አይደለም።

________ ሐሜት በኅብረተሰባችን ውስጥ ልማድ ሆኗል፣ በመሆኑም ይህን ለማስወገድ ለሥርዓት መገዛትን ማዳበር ይገባናል።

________ ስለሌላ ሰው የምንነግረውን አድማጩ መልሶ ላለማወራት ቃል ከገባ፣ ሐሜት ምንም ጉዳት አይኖረውም።

________ ሐሜት ከአንድነት ታላላቅ ጠላቶች መካከል አንዱ ነው።

________ ዘወትር ስለ ሌሎች ሰዎች የማውራት ልምድ ካለን፣ ወደ ሐሜት በቀላሉ ልንገባ እንችላለን።

________ በአካባቢ መንፈሳዊ ጉባዔ ውስጥ የኮሚቴ አባላትን ለመለየት የተለያዩ ሰዎች ችሎታዎች ለውይይት ሲቀርብ፣ ይህ ሐሜት ነው።

________ ለሐሜት የመገፋፋት ስሜት ሲሰማን፣ ስለ ገዛ ራሳችን ጉድለቶች ማስታወስ ይገባናል።

________ አንድ ሰው እምነቱን የሚጎዳ ነገር እያደረገ መሆኑን ስናውቅ፣ ከማኅበረሰቡ አባላት ጋር መወያየት ይገባናል።

________ አንድ ሰው እምነቱን የሚጎዳ ነገር እያደረገ መሆኑን ስናውቅ፣ ለአካባቢ መንፈሳዊ ጉባዔ ብቻ ማሳወቅ ይገባናል፡፡

________ ባለትዳር ጥንዶች አንዱ ከሌላው የሚሰውሩት ምስጢሮች ሊኖራቸው ስለማይገባ ስለሌሎች ሰዎች ጉድለቶች ቢነጋገሩ ስህተት አይደለም፡፡

## ምዕራፍ 9

መጀመሪያ ላይ እንደተገለጸው፣ የዚህ ክፍል ዓላማ፣ ተሳታፊዎች ከቅዱሳን ጽሑፎች በየዕለቱ ምንባቦችን ማንበብ እና በትርጉማቸው ላይ የማሰላሰል ልማድ ለማጎልበትና ለማጠናከር ለሚያደርጉት ጥረት ማገዝ ነው፡፡ የአምላክን ቃላት በየዕለቱ ጠዋትና ማታ ማንበብ ለመንፈሳዊ ዕድገት የሚረዳ የባሃኦላህ ትምህርት ነው፡፡ የሚከተለው ምንባብ ይህን ግዴታ በማሳካት የምንቀበለውን ፀጋዎች ያስታውሰናል፣ በመሆኑም ትውስታዎን እንዲያጠናክሩ ይበረታታሉ፦

**"ምስጢሮቹን ትገልፁ እና በጥልቀቶቹ ውስጥ የተደበቁትን ሁሉንም የጥበብ ዕንቁዎች ታገኙ ዘንድ፣ በቃላቴ ውቅያኖስ ውስጥ እራሳችሁን አስጥሙ፡፡"**[20]

ይህን ክፍል እንዳጠናቀቃችሁ፣ ከባሃኦላህ ጽሑፎች አንድ መጽሐፍ ማግኘት እና በየዕለቱ ከእሱ ለማንበብ ትፈልጉ ይሆናል፡፡ ሕቡዓተ ቃላት ጥሩ የመጀመሪያ ምርጫ ነው፡፡

## ማጣቀሻዎች


1. ባሃኦላህ፣ በሾጊ ኤፌንዲ የተጠቀሰ፣ የመለኮታዊ ፍትሕ ምፅዓት (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2006፣2018 የታተመ)፣ አንቀጽ 39፣ ገጽ 36—37፡፡
2. ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1983፣2017)፣ 139፣አንቀጽ 8፣ ገጽ 345፡፡
3. ባሃኦላህ፣ ኅቡዓተ ቃላት (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2003፣ 2012 የታተም)፣ ዓረብኛው ቁጥር 31፣ ገጽ 11፡፡
4. ዝኒ ከማሁ፣ ፋርስኛው ቁጥር 5፣ ገጽ 24፡፡
5. ዝኒ ከማሁ፣ ፋርስኛው ቁጥር 69፣ ገጽ 46፡፡
6. አብዱል—ባሃ፣ በሾጊ ኤፌንዲ የተጠቀሰ፣ የመለኮታዊ ፍትሕ ምፅዓት፣ አንቀጽ 40፣ ገጽ 39፡፡
7. ዝኒ ከማሁ፡፡
8. ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣ 136፣ አንቀጽ 6፣ ገጽ 336፡፡
9. ከኪታቢ አቅዳስ በኋላ የተገለጹ የባሃኦላህ ፅላቶች (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1988፣ 2005 የታተመ)፣ ቁጥር 9.5፣ ገጽ 138፡፡
10. ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣ 137፣ አንቀጽ 3፣ ገጽ 338፡፡
11. ዝኒ ከማሁ፣ 132፣ አንቀጽ 5፣ ገጽ 327፡፡
12. የአብዱል—ባሃ ቃል ኪዳንና ኑዛዜ (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1944፣ 2013 የታተመ)፣ ገጽ 26፡፡
13. ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣ 5፣ አንቀጽ 5፣ ገጽ 8፡፡
14. በኦክቶበር 16 እና 17 ቀን 1911 የተደረገ ንግግር፣ በፓሪስ የተደረጉ ንግግሮች ውስጥ የታተመ፡- በ1911 በአብዱል—ባሃ የተደረጉ ንግግሮች (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2006፣ 2016 የታተመ)፣ ቁጥር 1.7፣ ገጽ 6፡፡
15. በኦክቶበር 21 ቀን 1911 በአብዱል—ባሃ ከተደረጉ ንግግሮች፣ ዝኒ ከማሁ፣ቁጥር 6.7፣ ገጽ 22፡፡
16. ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣ 125፣ አንቀጽ 3፣ ገጽ 300፡፡
17. ኅቡዓተ ቃላት፣ ዓርረብኛ ቁጥር 27፣ ገጽ 10፡፡
18. ዝኒ ከማሁ፣ ፋርስኛው ቁጥር 44፣ ገጽ 37፡፡
19. ዝኒ ከማሁ፣ ዓረብኛ ቁጥር 26፣ ገጽ 10፡፡
20. ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣ 70፣ አንቀጽ 2፣ ገጽ 154፡፡



# ጸሎት

## ዓላማ

በጸሎት አስፈላጊነት ላይ ለማሰላሰል እና
በቋሚነት የመጸለይ ልምድን ለማዳበር

## ምዕራፍ 1

የሩሂ ተቋም ትምህርቶች የታቀዱት ተሳታፊዎች የአገልግሎት ጎዳና እንዲጓዙ ለማገዝ ነው። ይህን ጎዳና የምንጓዘው በሁለት እጥፍ ዓላማ ምክንያት ተነሳስተን ነው——በመንፈስና በአዕምሮ ለማደግ እንዲሁም ለኅብረተሰብ ለውጥ አስተዋፅዖ ለማበርከት። እነዚህ ሁለት የዓላማችን ገጽታዎች እርስበርስ የማይነጣጠሉ ናቸው። ባሃኡላህ በአንድ ምንባብ እንዲህ አጥብቆ ያሳስበናል፦

> **"በራሳችሁ ጉዳዮች ብቻ ራሳችሁን አትጥመዱ፤ ሃሳቦቻችሁ በነዚያ የሰውን ዘር ዕድሎች በሚያሻሽሉ እና የሰዎችን ልቦች እንዲሁም ነፍሶች በሚቀድሱ ነገሮች ላይ ያተኩሩ።"[1]**

እርሱ፣ በሌላ ምንባብም፣ ሲገልጽ፦

> **"...ሟች ሰዎች ከምንምነት ወደ ሕልውና ግዛት የመምጣታቸው ዓላማ፣ ለዓለም መሻሻል ይሠሩ ዘንድ እንዲሁም ተስማምተውና ተጣጥመው በጋራ እንዲኖሩ ነው።"[2]**

እርሱ፣ ከውስጣዊ ሁኔታችን በተገናኘ፣ እንዲህ ይገልፃል፦

> **"ንጹህ ልብ እንደ መስታወት ነው፤ እውነተኛዋ ፀሐይ በውስጡ ታንፀባርቅና የዘለዓለማዊው ንጋት ጎህ ይቀድ ዘንድ፣ ከአምላክ በቀር ከሁሉም ነገር በፍቅርና መላቀቅ መወልወያ አፅዱት። "[3]**

እንዲሁም አብዱል—ባሃ እንዲህ ይነግረናል፦

> **"የመለኮታዊ ስጦታዎች ተቀባዮች ትሆኑ ዘንድ ልባችሁ ንጹህ ፍላጎታችሁም ቅን መሆን አለበት።"[4]**

1. የሃሳቦቻችን እና ጉዳዮቻችን ትኩረት ምን ሊሆን ይገባል? ______________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

2. ከምንምነት ወደ ሕልውና ግዛት የመጣነው ለምን ዓላማ ነው? __________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

3. የልባችንን መስታወት በምን ልናፀዳ ይገባናል? ____________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

4. መለኮታዊ ስጦታዎችን የሚሰቡ አንዳንድ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው? ________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

5. ከሚከተሉት የትኞቹ እውነት ናቸው?

_____ በመጀመሪያ እራስዎን ሊንከባከቡ ይገባል፣ ከዚያ በኋላ ሌሎችን ሊንከባከቡ ይችላሉ።

_____ ሁልጊዜ ሌሎችን እየረዱ ከሆነ፣ የራስዎን ግቦች ማየት ይሳንዎታል።

_____ የራስዎ እጅግ ቅርብ ወዳጅ እራስዎ ነዎት።

_____ ዋናው ነገር ምን ደስተኛ እንደሚያደርጎት ማወቅ ነው።

_____ ሕልሞችዎን ይከተሉ፣ እነሱም ወደ ደስታ ይመሩዎታል።

_____ ማንንም እስካልጎዱ ድረስ፣ ምንም ቢሠሩ ምንም አይደለም።

_____ ጥሩ ነገር እስከሠሩ ድረስ፣ ፍላጎትዎ ራስወዳድ ቢሆን ምንም አይደለም።

## ምዕራፍ 2

የሁለት እጥፍ ዓላማችን ፅኑ ዕምነት ማዕከል ሁላችንም ክቡር ሆነን መፈጠራችን ነው። ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፦

**"የመንፈስ ልጅ ሆይ! ህብታም አድርጌ ፈጠርኩህ፣ ለምን ራስህን ወደ ድህነት ታወርዳለህ? ክቡር አደረግኩህ፣ ለምን ራስህን ታዋርዳለህ? ከዕውቀት ህላዌ ሕያውነትን ሰጠሁህ፣ ለምን ከእኔ በስተቀር ከሌላ የዕውቀት ብርሃን ትሻለህ? ከፍቅር አፈር ሠራሁህ፣ እንዴት ራስህን ከሌላ ጋር ታወዳጃለህ? ዕይታህን ወደ ራስህ መለስ አድርግ፣ በውስጥህ ኃያል፣ ኃይል የተመላሁና በጋዛ ራሱ ነዋሪ ሆኜ ቆሜ ታገኘኝ ዘንድ።"[5]**

ከሥር ያሉትን ባዶ ቦታዎች መሙላት በዚህ ምንባብ ላይ ለማሰላሰል ይረዳዎታል።

"የመንፈስ ልጅ ሆይ! ____________________ አድርጌ ፈጠርኩህ፣ ለምን ራስህን ወደ

______________________________?______________ አደረግኩህ፣

ለምን ራስህን________________?______________________________

______________________________ሕያውነትን ሰጠሁህ፣ለምን__________

በስተቀር ከሌላ______________________________________________?

____________________ አፈር ______________________________፣

እንዴት ራስህን ______________ጋር____________________________?

________________________ ወደ ____________________መለስ አድርግ፣

በውስጥህ ________________________፣__________________________ና

*ታገኘኝ ዘንድ።”*

*የነፍሶቻችን ክቡርነት እውን ይሆኑ ዘንድ፣ ወደ ሕልውናችን ምንጭ መዞር እና ከእርሱ የዕውቀት ብርሃን መሻት አለብን። ይህን የመቀዳጀት እጅግ አሳማኝ መንገዶች አንዱ ጸሎት ነው። የእምነቱ ሞግዚት የሆነው ሾጊ ኤፌንዲ እንደሚነግረን፣ የጸሎት ዋና ግብ “መንፈሳዊ ባህርያትንና ኃይሎችን በመቀዳጀት፣ የግለሰብ እና ኅብረተሰብ መጎልበት ነው። መጀመሪያ መመገብ ያለበት የሰው ነፍስ ነው። ይህም መንፈሳዊ ምግብ በእጅጉ በጸሎት ሊቀርብ ይችላል።”[6]*

## ምዕራፍ 3

*አምላክ ሁሉን አዋቂው፣ ፍፁም ጠቢቡ ነው። የፈጠረን እርሱ ነው በልባችንም ውስጥ ምን እንዳለና ለኛ የሚበጀንን ያውቃል። ጸሎቶቻችንን አይፈልግም። ታዲያ ለምን እንጸልያለን?*

*አብዱል—ባሃ ሲገልጽ፦*

***“በእጅግ በጣም ከፍተኛው ጸሎት፣ሰዎች ጸሎት የሚያደርሱት ለአምላክ ፍቅር ብቻ ሲሉ እንጂ፣ እርሱን ወይም ሲኦልን በመፍራት፣ ወይም ለፀጋ ወይም መንግሥተ ሰማይን ተስፋ አድርገው አይደለም። ... አንድ ሰው በሌላ ሰው ልጅ ፍቅር ሲረታ፣ የተወዳጁን ስም ከማንሳት ሊቆጠብ አይቻለውም። አምላክን ለማፍቀር የበቃውንማ የእርሱን ስም ከማንሳት መከልከል የቱን ያህል የበለጠ አስቸጋሪ ነው። ...መንፈሳዊ ሰው አምላክን በማስታወስ በቀር በሌላ በምንም ደስታን አያገኝም።”[7]***

*እርሱ፣ለጥያቄም ምላሽ ሲሰጥ፣ እንዲህ ያብራራል፦*

***“አንድ ወዳጅ ሌላውን ቢያፈቅር፣ያንን ለመግለጽ መሻት ተፈጥሮአዊ አይደለምን? ምንም እንኳ ወዳጁ ስለፍቅሩ የሚያውቅ መሆኑን ቢያውቅም፣ሊነግረው አይፈልግምን?... አምላክ የልቦችን ሁሉ ምኞቶች የሚያውቅ መሆኑ እውነት ነው፤ ነገር ግን የመጸለይ ስሜት ግፊት ሰው ለአምላክ ካለው ፍቅር የሚመንጭ ተፈጥሮአዊ ፍላጎት ነው።”[8]***

1. *የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ያሟሉ፦*

*ሀ.* ________________ *ጸሎት፣* ________________

*ለአምላክ* ________________ *ብቻ ስንል እንጂ፣ እርሱን*

*ወይም* ________________ *በመፍራት፣ ወይም* ________ *ወይም*

________ ________ *ተስፋ አድርገን አይደለም።*

*ለ. በሌላ ሰው ልጅ* ________ *ስንረታ፣ የ* ________________

________________ *ከማንሳት ልንቆጠብ* ________________ ።

________________ *የበቃውንማ የእርሱን ስም*

*ከ* ________ *መከልከል የቱን ያህል የበለጠ* ________ *ነው።*

ሐ. መንፈሳዊ ሰው አምላክን ________________________________ በቀር በሌላ በምንም ________________________ አያገኝም።

2. ለምን እንጸልያለን? ______________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

3. "አምላክን ማስታወስ" የሚለው ሐረግ ምን ማለት ነው? ___________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

4. ሌላ ሰውን የሚያፈቅር አንድ ሰው እጅግ ፅኑ እሾት ምንድን ነው? ______________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

5. የመጸለይ ስሜት ግፊት ከምን ይመነጫል? ____________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

## ምዕራፍ 4

በባሃኡላህ በተገለፀ ጸሎት ውስጥ እንዲህ እናነባለን፦

**"ጸሎቱ ውበትህን እንዳላይ የጋረደኝን ግርዶሽ የሚያንድ እሳትና ወደ ቅርበትህም ውቅያኖስ የሚመራኝ ብርሃን እንዲሆንልኝ ... እማጸናለሁ።"[9]**

በዚያው ተመሳሳይ ጸሎት ውስጥ አምላክን እንማጸናለን፦

**"ጌታዬ ሆይ! ጸሎቴን፣ ሉዓላዊነትህ እስካለ ድረስ ለመኖርና በዓለማትህም እያንዳንዱ ዓለም ስምህን ላወሳበት የምችልበት፣ የሕያው ውሃዎች ምንጭ አድርግልኝ።"[10]**

1. ጸሎት በእሳት የሚመሰለው በምን መልኩ ነው? ምንን ይፈጃል/ይጨርሳል? ___________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

2. ከአምላክ የጋረዱንን አንዳንድ ግርዶሾች ይጥቀሱ፦ _______________________

3. ጸሎት በብርሃን ሊመሰል ይችላልን? ወዴት ይመራናል? ______________________________

4. ጸሎት በሕያው ውሃዎች ምንጭ ሊመሰል ይችላልን? በነፍሳችን ላይ ምን ይለግሰናል? _______

## ምዕራፍ 5

የሚከተሉትን የአብዱል—ባሃ ቃላት አንብባችሁ አሰላስሉበት፦

**"በፍጥረት ዓለም ከጸሎት ይበልጥ ጣፋጭ የሆነ ምንም ነገር የለም። ሰው በጸሎታዊ ሁኔታ ውስጥ መኖር አለበት። እጅግ በጣም የተባረከ ሁኔታ የጸሎትና የተማፅኖ ሁኔታ ነው። ጸሎት ከአምላክ ጋር መነጋገር ነው። ከአምላክ ጋር ከመነጋገር በቀር ሌላ እጅግ በጣም ታላቅ ግብ ወይም እጅግ በጣም ጣፋጭ ሁኔታ የለም። መንፈሳዊነትን ይፈጥራል፣ማስተዋልንና መንግሥተ ሰማያዊ ስሜቶችን ይፈጥራል፣የመንግሥተ ሰማያዊ አዲስ መስህቦችን ያመጣል እንዲሁም የከፍተኛ ንቃተ-ኅሊና ተቀባይነቶችን ይከስታል።"[11]**

1. በፍጥረት ዓለም ውስጥ እጅግ በጣም ጣፋጩ ሁኔታ ምንድን ነው? ______________________

2. "የጸሎት ሁኔታ" የሚለው ሐረግ ምን ማለት ነው? ___________________________________

3. በጸሎት ከሚፈጠሩ መልካም ባሕርያት አንዳንዶቹን ይጥቀሱ፦ ___________________________

4. በእነዚህ ጥቂት ምዕራፎች ውስጥ ያጠናችሁትን ጥቅሶች ይከልሱ እንዲሁም በጸሎት ተፈጥሮ ላይ አምስት ሐረጎች ይጻፉ።

_ ጸሎት ______________________________ ነው።

_ ጸሎት ______________________________ ነው።

_ ጸሎት ______________________________ ነው።

_ ጸሎት ______________________________ ነው።

_ ጸሎት ______________________________ ነው።

## ምዕራፍ 6

የሚከተሉትን የባሃኦላህ ቃላት ያንብቡና ያሰላስሉባቸው፦

**"አገልጋይ ሆይ! የዝማሬህ ጥዑምነት የራስህን ንፍስ እንዲያቀጣጥልና የሁሉንም ሰዎች ልቦች እንዲስብ፣የተቀበልካቸውን የአምላክ ጥቅሶች፣ እነዚያ ወደ እርሱ የቀረቡት እንዳዜሙት አዚማቸው። በአምላክ የተገለፁትን ጥቅሶች ማንም ሰው ብቻውን በክፍሉ ውስጥ ሆኖ ቢደግም፣ የፍፁም ኃያሉ አሰራጭ መላዕክት፣ ከአፉ የሚወጡትን መዓዛዎች በሰፊው በሁሉም አቅጣጫ ያሰራጩቸዋል፤ የእያንዳንዱም ፃድቅ ሰው ልብ ትርታ እንዲጨምር ያደርጋሉ። ምንም እንኳ በመጀመሪያ ውጤቱን ባይገነዘበውም፣ የተሰጠው ፀጋ ረድዔት ፈጥኖም ሆነ ዘግይቶ በነፍሱ ላይ የመለወጥ ኃይሉን ማሳየቱ የማይቀር ነው። በእርሱ የኃይልና የጥበብ ምንጭ በሆነው ፈቃድ አማካይነት የአምላክ ግልፀት ምሥጢራት በዚህ ሁኔታ ታውጀዋል።"**[12]

1. "አዚም" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ______________________________

______________________________

______________________________

2. የአምላክን ጥቅሶች እንዴት ማዜም ይገባናል? ______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

3. "ድገም" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ______________________________

______________________________

______________________________

4. "ማሰራጨት" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ______________________________

______________________________

5. የዝማሬያችን ጥዑምነት  በገዛ ራሳችን ነፍሶች ላይ ምን ውጤት አለው? ________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

6. የዝማሬያችን ጥዑምነት በሌሎች ልቦች ላይ ምን ውጤት አለው? ______________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

## ምዕራፍ 7

በባሃኦላህ ከተገለፁት የሚከተሉትን ሁለት ምንባቦች በቃል ለመያዝ ትፈልጉ ይሆናል፦

**"አምላኬ፣ አምላኬ ሆይ! ሰማያትና ምድርን የከበበውን ፈቃድህን ተመልከት እንጂ ምኞቶቼንና ድርጊቶቼን አትመልከት። በፍጹም ታላቁ ስምህ፣ አንተ የብሔሮች ሁሉ ጌታ ሆይ! አንተ የፈለግኸውን ብቻ ፈልጌአለሁ፣ የምታፈቅረውንም ብቻ አፈቅራለሁ።"[13]**

**"ወደ አንተ የቀረቡት የሚያቀርቡት ምስጋና ወደ ቅርበትህ ሰማይ ከመውጣት፣ወይም የእነዚያ ለአንተ ያደሩት ሰዎች ልቦች አዕዋፋት ወደ መንበርህ በር ከመድረስ በጣም ከፍ ያልክ ነህ። አንተ ከባሕርያት ሁሉ የነፃህ፣ ከስሞችም ሁሉ በላይ ቅዱስ መሆንህን እመሰክራለሁ። ከአንተ ፍፁም ከላቅኸው፣ፍፁም ክብር ከተመላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም።"[14]**

## ምዕራፍ 8

አብዱል—ባሃ ሲገልጽ፦

**"መጸለይና ከአምላክ ዕገዛን መሻት፣ የእርሱንም ዕርዳታ መማጸንና መለመን የአገልጋዩ ግዴታ ነው። የአገልጋይነት ማዕረግ እንደዚህ ይሆናል፣ ጌታም ከእርሱ ፍፁም ጥበብ ጋር የሚስማማ፣ እርሱ የፈለገውን ማንኛውንም ያዛል።"[15]**

እርሱ፣ እንዲህም ያብራራል፦

**"መንፈስ ተፅዕኖ አለው፤ ጸሎት መንፈሳዊ ውጤት አለው። ስለዚህ፣'አምላክ ሆይ! ይህን ሕመምተኛ ፈውስ!' በማለት እንጸልያለን። ምናልባት አምላክ መልስ ይሰጥ ይሆናል። የሚጸልየው ማንነት ልዩነት ያመጣልን? ጸሎቱ አስቸኳይ ከሆነ፣ አምላክ ለእያንዳንዱ አገልጋይ ጸሎት መልስ ይመልሳል። የእርሱ ምህረት ሰፊ፣ወሰን አልባ ነው። እርሱ የሁሉንም አገልጋዮቹን ጸሎቶች ይመልሳል። የዚህን ተክል ጸሎት መልስ ይሰጣል። ተክሉ በስውር መንገድ፣ 'አምላክ ሆይ! ዝናብ ላክልኝ!' በማለት ይጸልያል። አምላክ ለጸሎቱ መልስ ይሰጥና ተክሉ ያድጋል። አምላክ ለማንም መልስ ይሰጣል።"[1]**

በጸሎቶቻችን ፍላጎታችንን እንዲያሟላልን አምላክን መጠይቃችን ተፈጥሮአዊ ነው። ስለዚህ ለጤናችን እና ለምንወዳቸው ሰዎች ጤና እንጸልያለን፣ለቤተሰቦቻችን መንፈሳዊና ቁሳዊ ዕድገት እንጸልያለን፣ ለመመሪያም እንጸልያለን። በአገልግሎት ጎዳና ላይ ጥንካሬን፣ እምነትን፣ እና ማረጋገጫን እንጠይቃለን። በዕርግጥ ወደ አምላክ ስንጸልይ፣ የሕይወት ግባችን ከእርሱ ፈቃድ ጋር መስማማቱን ማስታወስ ይገባናል። ስለዚህ የእርሱ ፈቃድ እንዲፈጸምና ለእርሱም እራሳችንን ለማስገዛት ዝግጁ እንድንሆን መጸለይ አለብን። የሚከተሉትን የአብዱል—ባሃ ቃላት በቃል ለመያዝ ጥረት ካደረጉ፣ ሁሌም የደስታና የማረጋገጫ ምንጭ በመሆን ያገለግላሉ፦

> **"አንተ ፊትህን ወደ አምላክ የምታቀና ሆይ! ዓይኖችህን በሁሉም ሌሎች ነግሮች ላይ ጨፍነህ ለንዑዱ አምላክ ዓለም ግለጣቸው። የምትሻውን ማንኛውም ነገር ከእርሱ ብቻ ጠይቅ፤ የምትፈልገውን ማንኛውንም ነገር ከእርሱ ብቻ ፈልግ። በአንዲት ዕይታ መቶ ሺህ ተስፋዎችን ይሰጣል፣ በጨረፍታ ዕይታም መቶ ሺህ የማይድኑ ደዌዎችን ይፈውሳል፣ በአንዲት የይሁንታ ምልክትም በእያንዳንዱ ቁስል ላይ መድሃኒት ያደርጋል፣ በቅፅበታዊ ዕይታም ልቦችን ከኃዘን ሰንሰለት ነፃ ያወጣል። የፈለገውን ያደርጋል፣ ምንስ ምርጫ አለን? ፈቃዱን ይፈጽማል፣ የፈለገውን ነገር ያዛል። ስለዚህ በመታዘዝ መንፈስ ራስህን መድፋትና እምነትህን በፍፁም መሓሪው ጌታ ላይ ማድረግ ይሻልሃል።"[17]**

## ምዕራፍ 9

እስካሁን ካጠናነው ሁሉ ነገር፣ በጸሎት ወደ አምላክ መዞር የመንፈሳዊ ሕይወት ወሳኝ መስፈርት እንደሆነ ግልፅ ነው። በተለይ ጠዋት ከእንቅልፍ ከተነሳን በኋላ ወዲያው እንዲሁም ማታ ከመተኛታችን በፊት ወደ አምላክ መጸለይ እንዴት ጣፋጭ ነው። በየዕለቱ ጸሎት በማድረግ የምናሳልፈው ጊዜ እና የጸሎቶች ብዛት በፍላጎቶቻችንና መንፈሳዊ ጥማታችን ላይ ይመረኮዛል። በማንኛውም ሁኔታ በባሃኡላህ፣ ባብ፣ እና አብዱል—ባሃ ከተገለፁት ብዛት ካላቸው ጸሎቶች ለመምረጥ እንችላለን። ባሃኡላህ ደግሞ ሶስት ዕለታዊ የግዴታ ጸሎቶችን ገልጿል፡፡ ሾጊ ኤፌንዲ እንዲህ ይላል፦

> **"ዕለታዊ የግዴታ ጸሎቶች በቁጥር ሶስት ናቸው። እጅግ አጭሩ አንድ አንቀጽ ያለው ሲሆን በሃያ አራት ሰዓታት አንድ ጊዜ ቀትር ላይ ሊደገም ይገባል። መካከለኛው 'ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ጌታ ምስክር ነው' በሚሉት ቃላት የሚጀምረው፣ በቀን ሶስት ጊዜ ጠዋት፣ ዕኩለ ቀን እና ማታ መደገም አለበት። ይህ ጸሎት በተወሰኑ አካላዊ እንቅስቃሴዎችና ምልክቶች ይታጀባል። ከሶስቱ እጅግ ስፋት ያለው ረጅሙ ጸሎት፣ አንድ ሰው ለማድረግ በሚሻበት ማንኛውም ሰዓት፣ በየሃያ አራት ሰዓታት ውስጥ አንድ ጊዜ ብቻ ሊደገም ይገባል።**
>
> **"አማኙ ከእነዚህ ሶስት ጸሎቶች አንዱን ለመምረጥ ፍፁም ነፃ ነው፣ነገር ግን ከነዚህ አንዱን አብረውት በሚሄዱ የተወሰኑ መመሪያዎች መሠረት የመድገም ግዴታ አለበት።"[18]**
>
> እርሱ፣ በመቀጠልም፦
>
> **"እነዚህ ዕለታዊ የግዴታ ጸሎቶች፣ ተለይተው ከተጠቀሱት እንደ ፈውስ ጸሎት፣ መልዕክተ አህመድ፣ ያሉት ጥቂት ጸሎቶች ጋር ተጣምረው በባሃኡላህ ልዩ ኃይልና ትርጉም ስለተሰጣቸው፣ እንዲህ ባለ መልኩ መቀበል ይገባል፣ አማኞችም በእነርሱ አማካይነት ይበልጥ ከአምላክ ጋር ወደ መቋረብ እንዲጠጉ እና ለሕግጋቱና ለመመሪያዎቹ ይበልጥ በተሟላ ሁኔታ**

**ራሳቸውን ለማስገዛት ይችሉ ዘንድ፣ በማያጠያይቅ እምነትና በልበ ሙሉነት መድገም አለባቸው:: ..."[19]**

በባሃኦላህ የተገለፁት ሶስቱ የግዴታ ጸሎቶች በግል የሚደረጉ ናቸው:: ዕለታዊ የግዴታ ጸሎት የሚደገምባቸው እንደ አንዳንድ በጋራ ተሰባስበው የሚደገሙ ሥራዓተ አምልኮ ዓይነት በባሃኢ እምነት ውስጥ የለም:: በባሃኢ ሕግ የተደነገገ ብቸኛ በጋራ ተሰባስበው የሚደገም ሥርዓተ አምልኮ የሙታን ጸሎት ነው:: ይህ ከግብዓተ መሬት በፊት ከነዚያ ከተገኙት መካከል በአንዳቸው የሚደገም ሲሆን፣ የቀሩት ደግሞ በፀጥታ ቆመው ይታደማሉ::

1. "የግዴታ" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? ____________________

____________________

2. ባሃኦላህ ምን ያህል ዕለታዊ የግዴታ ጸሎቶችን ገልጿል? ____________________

3. ሶስቱንም ጸሎቶች በየዕለቱ መድገም ይገባናልን? ____________________

____________________

4. ረጅሙን የግዴታ ጸሎት ለማለት ከመረጥን፣ በየዕለቱ ምን ያህል ጊዜ መድገም ይገባናል? ____

____________________

5. መካከለኛውን የግዴታ ጸሎት ለማለት ከመረጥን፣ ምን ያህል ጊዜ? ____________________

____________________

6. አጭሩን የግዴታ ጸሎት ለማለት ከመረጥን፣ ምን ያህል ጊዜ? ____________________

____________________

7. የተለየ ኃይል ያላቸውን አንዳንድ ጸሎቶች ይግለጹ፦ ____________________

____________________

8. አጭሩን የግዴታ ጸሎት እስካሁን ካልሞከሩት፣ በቃልዎ ይያዙት፦

**"አምላኬ ሆይ፣ አንተን እንዳውቅና እንድሰግድልህ እንድፈጠርከኝ እመሰክራለሁ:: በዚህ ሰዓት የእኔን ደካማነትና የአንተን ኃያልነት፣ የእኔን ምስኪንነትና የአንተን ሀብታምነት አረጋግጣለሁ::**

**"ከአንተ በአደጋ ጊዜ ረዳት፣ በገዛ ራሱም ነዋሪ ከሆንከው በስተቀር ሌላ አምላክ የለም::"[20]**

9. በዚህ ጸሎት ምን እናረጋግጣለን? ____________________

____________________

____________________

____________________

## ምዕራፍ 10

የግዴታ ጸሎትን ሕግ በመተግበራችን ከምናገኘው ቡራኬዎች እና ሌሎች ጸሎቶችን በግል ከማድረግ ከምናገኘው መበልፀግ በተጨማሪ፣ በትልቅም ሆነ አነስተኛ ስብሰባዎች ጸሎቶች ሲደገሙ ስንሰማ ነፍሶቻችን ይነቃቃሉ። ባሃኦላህ እንዲህ ይነግረናል፦

> **"በላቀ ሐሴትና ወዳጅነት በጋራ በመሰባሰብ በመኃሪው ጌታ የተገለፁትን ጥቅሶች ድገሟቸው። ይህን በማድረግ የእውነተኛ ዕውቀት በሮች ለውስጣዊ ሕላዌያችሁ ይገለፃል፣ እንዲሁም ነፍሶቻችሁ በፅናት ሲታደልና ልባችሁም በአንፀባራቂ ደስታ ሲሞላ ይሰማችኋል።"[21]**

በዓለም ዙሪያ ወዳጆችና ጎረቤታሞች በጋራ በመሆን ከአምላክ ጋር ለማውጋት የጸሎተ ሱታፌ ስብሰባዎች የሚያካሂዱት በሺዎች እየተባዙ መሆናቸውን ማወቃችን ትልቅ ደስታ ያጎናጽፈናል። የአለም አቀፍ ቤተ-ፍትህ ሲጽፍ፦

> **"የጸሎተ ሱታፌ ስብሰባዎች ማንም ነፍስ ገብታ፣የሰማያዊ መዓዛዎችን ልታሸትበት፣ የጸሎትን ጣፋጭነት ልታጣጥምበት፣ በሚፈጥር ቃሉም ላይ ልታሰላስልበት፣ በመንፈስ ክንፎች ልትንገዝበትና፣ ከተወዳጁ ጋር ልታወጋበት የምትችልበት ወቅቶች ናቸው። በተለይ እንዲህ ባለ በተፈጥሮ የሚከሰቱ የላቁ መንፈሳዊ ጭውውቶች ወቅትና በዚያም 'የሰው ልብ ከተማ' በሚከፈትባቸው፣ የወዳጅነትና የጋራ ዓላማ ስሜቶች ይፈልቃሉ።"[22]**

ለጸሎት ስሜት ውስጣችን ሲነሳሳ፣ አዕምሮአችንን ከዚህ ዓለም ነገር ለማፅዳት ለጥቂት ጊዜ በፀጥታ እንቆያለን። እየጸለይን ሳለ ሃሳባችንን በአምላክ ላይ እናደርጋለን። ጸሎቶች ከደገምን በኋላ፣ ለጥቂት ጊዜ በፀጥታ መቆየትና ወደ ሌላ ተግባር በችኮላ መግባት አይኖርብንም። በስብሰባዎችም ውስጥ በሌሎች ሰዎች ጸሎቶች ሲቀርቡ በተመሳሳይ ማዳመጥ አስፈላጊ ነው። እንዲህ ባሉ ጊዜያት እኛ እየደገምናቸው እንዳለን ያህል፣ ጸሎታዊ ሁኔታን እንከተላለን እንዲሁም ቃላቶቹንም በቅርበት እንከታተላለን።

1. የአምላክ ጥቅሶችን ስንደግም በምን ዓይነት መንፈስ በጋራ መሰባሰብ ይገባናል? ____________
   ________________________________________________
   ________________________________________________

2. የአምላክን ጥቀሶች ለመድገም በጋራ መሰባሰባችን ምን ተፅዕኖ ይኖረዋል? ______________
   ________________________________________________
   ________________________________________________
   ________________________________________________

3. የጸሎተ ሱታፌ ስብሰባዎች ማንም ነፍስ
   ____________________፣
   ________________________________________፣
   __________________________________________፣
   ___________________________________________፣

_________________________________________________________________፣እና

_________________________________________________________________ናቸው።

4. በጸሎተ ሱታፌ ስብሰባዎች ምን ዓይነት ስሜቶች ይፈልቃሉ? ___________________________

_________________________________________________________________

5. በጸሎተ ሱታፌ ስብሰባዎች ላይ በተፈጥሮ የሚከሰቱ የላቁ መንፈሳዊ ጭውውቶች ተፅዕኖ ምንድን ነው? ____________________________________________________

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

6. ለብቻም ሆነ በጋራ ለጸሎት ስንሰባሰብ ማሳየት ስለሚገባን የአክብሮት ሁኔታ ጥቂት ቃላት ፃፉ።

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

## ምዕራፍ 11

በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያው ክፍል በየዕለቱ ከቅዱሳን ጽሑፎች ምንባቦች የማንበብና በትርጉማቸው ላይ የማሰላሰል ልምድ ላይ አተኩሯል። እዚህ በጸሎት ጠቀሜታ ላይ አሰላስላችኋል፣ በውጤቱም በየዕለቱ የመጸለይን ልምድ አዳብራችኋል። ቀዳሚው ምዕራፍ የማኅበረሰብ አምልኮን አስፈላጊነት ወደ ትኩረታችሁ አምጥቷል። ከፈለጋችሁ እስካሁን ያጠናችሁት ሁሉ፣ በአገልግሎት ጎዳና ላይ የመጀመሪያ ተግባር ለማከናወን አዘጋጅቷችኋል፦ የጸሎተ ሱታፌ ስብሰባ ማስተናገድ።

እንደመነሻ፣ በዛ ያሉ ጸሎቶችን በቃላችሁ ለማጥናት እና ለጥቂት ወዳጆች ለማካፈል ዕድል ማግኘት ትፈልጉ ይሆናል። ከዚያ ጎን ለጎን በማኅበረሰባችሁ ውስጥ ቢያንስ አንድ ጸሎት ሱታፌ ስብሰባ መካፈልና ከቆራጥ ደጋፊዎች መካከል አንዱ መሆናችሁን ልታረጋግጡ ትችላላችሁ። ከዚያ በሂደት ወዳጆቻችሁን፣ የቤተሰብ አባሎቻችሁን፣ ጎረቤታችሁን ለጸሎትና ወዳጅነት በቋሚነት ለመሰብሰብ በመጋበዝ እራሳችሁ የጸሎተ ሱታፌ ስብሰባ አስተናጋጅ ለመሆን ልትወስኑ ትችላላችሁ። የዚህ ኮርስ ሁለት ወይም ሦስት ተሳታፊዎች በጋራ እንደዚህ ያለ የጸሎተ ሱታፌ ስብሰባ መጀመር ያልተለመደ አይደለም።

ልትገምቱ እንደምትችሉት፣ የጸሎተ ሱታፌ ስብሰባ እንዴት እንደሚዘጋጅ ምንም ቀመር የለውም:: ነገር ግን በትክክል ሁሉም በታወቀ መንፈሳዊ ሁኔታ ውስጥ ወዳጆች ጸሎቶች የሚያደርሱበት፣ ከቅዱሳን ጸሐፎች ምንባቦች የሚነበቡበት፣እና አነቃቂ ጭውውቶች የሚካሄድበት ስብሰባ ነው:: ጸሎተ ሱታፌ ስብሰባን ከማስተናገድ አግባብ፣ ስለሚከተሉት ሃሳቦች ጥቂት ቃላት መናገር ትችላላችሁ?

የጋለ እና ፍቅር የተመላው ግብዣ ማስተላለፍ፡- ______________________________

ጋባዥ ድባብን/ሁኔታን መፍጠር፡-______________________________

የአምልኮ ድባብን/ሁኔታን መጠበቅ፡-______________________________

ደስታ የተላበሰ ወዳጅነትን ማራመድ፡-______________________________

መንፈሳዊ መነቃቃትን የሚያመጡ ጭውውቶች ማበረታታት፡- ______________________________

## ማጣቀሻዎች


1. ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣1983፣2017)፣43፣አንቀጽ 3፣ ገጽ 105።

2. ባሃኦላህ፣በ'ትረስትምርዝነስ' ውስጥ፡ ከባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች የተውጣጡ ጥንቅር፣ በዓለም አቀፍ ቤተ ፍትህ የምርምር ክፍል የተጠናቀረ (ለንደን፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1987)፣ ቁጥር 21፣ ገጽ 5።

3. የመስኮታዊው ተወዳጅ ጥሪ፡- የባሃኦላህ የተመረጡ መንፈሳዊ ረቂቅ ሥራዎች (ሃይፋ፡- የባሃኢ ዓለም ማዕከል፣ 2018)፣ ቁጥር 2.43፣ ገጽ 31።

4. በሜይ 5 1912 ከተሰጠ ንግግር፣ በዓለም ሰላም እወጃ ውስጥ የታተመ፡ በ 1912 የዩናይትድ ስቴትስና ካናዳ ጉብኝቱ ወቅት በአብዱል—ባሃ የተደረጉ ንግግሮች (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት፣ 2012)፣ ገጽ 127።

5. ባሃኦላህ፣ ኅቡዓተ ቃላት (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2003፣ 2012 የታተመ)፣ ዓረብኛው ቁጥር 13፣ ገጽ 6—7።

6. ሾጊ ኤፌንዲን በመወከል በዲሴምበር 8 1935 ከተጻፈ ደብዳቤ፣ በጸሎትና አምልኮአዊ ሕይወት ውስጥ የታተመ፡-ከባሃኦላህ፣ ባብ፣እና አብዱል—ባሃ ጽሑፎች እንዲሁም ከሾጊ ኢፌንዲ እና የዓለም አቀፍ ቤተ ፍትህ ደብዳቤዎች የተውጣጣ ጥንቅር፣ በዓለም አቀፍ ቤተ ፍትህ የምርምር ክፍል የተጠናቀረ (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት፣ 2019)፣ ቁጥር 71፣ ገጽ 31።

7. የአብዱል—ባሃ ቃላት፣ በጄ. ኢ. ኤስለሞንት የተጠቀሰ፣ ባሃኦላህ እና አዲሱ ዘመን፡- የባሃኢ እምነት መግቢያ (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2006፣2017)፣ ገጽ 106።

8. ዝኒ ከማሁ።

9. ባሃኦላህ፣ በባሃኢ ጸሎቶች ውስጥ፡- በባሃኦላህ፣ ባብ፣ እና አብዱል—ባሃ ከተገለጹ ጸሎቶች የተመረጠ (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2002፣2017)፣ ገጽ 7—8።

10. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 9።

11. የአብዱል—ባሃ ቃላት፣ ስታር ኦፍ ዘ ዌስት ውስጥ የተጠቀሰ፣ ቮልዩም 8፣ ቁጥር 4 (ሜይ 17 1917)፣ ገጽ 41።

12. ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣ ቁጥር 136፣አንቀጽ 2፣ ገጽ 334፤ በተጨማሪም በባሃኢ ጸሎቶች፣ ገጽ 3።

13. ባሃኦላህ፤ ባሃኢ ጸሎቶች ውስጥ፣ ገጽ 8—9።

14. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 12።

15. አብዱል—ባሃ፣ በጸሎትና አምልኮአዊ ሕይወት (ውስጥ የታተመ)፣ ቁጥር 24፣ ገጽ 7።

16. በሜይ 5 1912 ከተሰጠ ንግግር፣ በዓለም ሰላም እወጃ ውስጥ የታተመ፡- በ 1912 የዩናይትድ ስቴትስና ካናዳ ጉብኝቱ ወቅት በአብዱል—ባሃ የተደረጉ ንግግሮች ገጽ 345።

17. ከአብዱል—ባሃ ቀዱሳን ጽሑፎች የተመረጡ (ዊልሜት፡- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2010፣ 2015)፣ ቁጥር 22.1፣ ገጽ 75—76።

18. ሾጊ ኤፌንዲን በመወከል በጄንዋሪ 10 1936 ከተጻፈ ደብዳቤ፣ በጸሎትና አምልኮአዊ ሕይወት ውስጥ የታተመ፣ ቁጥር 61፣ገጽ 25።

19. ሾጊ ኤፌንዲን በመወከል በጄንዋሪ 10 1936 ከተጻፈ ደብዳቤ፣ በባሃኢ ጸሎቶች ውስጥ የተጠቀሰ፣ ገጽ 301።

20. ባሃኦላህ፣ በባሃኢ ጸሎቶች ውስጥ (የታተመ)፣ ገጽ 4።

21. ባሃኦላህ፣ በጸሎትና አምልኮአዊ ሕይወት ውስጥ (የታተመ)፣ ቁጥር 68፣ ገጽ 29።

22. ከዲሴምበር 29 2015 መልዕክት፣ የትግባር አውታር ውስጥ የታተመ፡- የዓለም አቀፍ ቤተ ፍትህ የተመረጡ መልዕክቶችና ተጨማሪ ጽሑፎች፣ 2006—2016 (ዌስት ፓልም ቢች፡- ፓልባራ ኅትመቶች፣ 2017)፣ ቁጥር 35።49፣ ገጽ 232።



# ሕይወት እና ሞት

### ዓላማ

ሕይወት የዚህን ዓለም ለውጦችና አጋጣሚዎች ብቻ
እንደማያካትት ይልቁንም ትክክለኛ ትርጉሙን
የሚቀዳጀው በነፍስ ዕድገት ውስጥ
መሆኑን ለመረዳት

## ምዕራፍ 1

የሰው ነፍስ ከቁስ አካልና ከተፈጥሮአዊ ዓለም በላይ የላቀች ናት። አብዱል—ባሃ ከንግግሮቹ በአንዱ ሲገልጽ፦

> **"እነዚህ ቁሳዊ አካላት ከአተሞች የተገነቡ ናቸው፤ እነዚህ አተሞች መለያየት ሲጀምሩ መፍረስ ይጀምራል፣ ከዚያም ሞት ብለን የምንጠራው ይመጣል። ...**
>
> **"ከነፍስ አኳያ ይህ የተለየ ነው። ነፍስ የንጥረነገሮች ቅንብር አይደለችም፣ከብዙ አተሞች የተገነባችም አይደለችም፣ አንድ የማትከፋፈል ስነ ቁስ/ህላዌ ናት ስለሆነም ዘለዓለማዊ ናት። ከቁሳዊ የአፈጣጠር ሥርዓት ሙሉበሙሉ የተለየች ናት፤ ዘለዓለማዊ ናት!"[1]**

1. "የተገነባ" ማለት ምን ማለት ነው? ______________________________________________

 ____________________________________________________________________

2. የሰው ነፍስ እንደ ቁሳዊ አካላት ከተለያዩ ንጥረነገሮች የተገነባ ነውን? ____________________

 ____________________________________________________________________

3. የሰው ነፍስ ቁሳዊ ነገር ነውን?_____________________________________________

 ____________________________________________________________________

## ምዕራፍ 2

ሞግዚቱን በመወከል የተጻፈ ደብዳቤ "የሰው ነፍስ ወደ ሕልውና የምትመጣው በፅንስ ወቅት ነው"[2] በማለት ይገልጻል። ስለ "ፅንስ" ትርጉም ለቀረበ ጥያቄ ዓለም ዓቀፍ ቤተ-ፍትህ ምላሽ ሲሰጥ፦

> **"ፅንስ" ተብሎ የተገለፀውን ስነ-ሕይወታዊ/ 'ባዮሎጂካል' ወቅት እና የኩነቱን ተፈጥሮ በትክክል የሚገልፅ ከባሃኢ ቅዱሳን ጽሑፎች ምንም አልተገኘም። በሕክምና አቀራረብም ቢሆን የቃሉ አጠቃቀም የተዛነፈ ሆኖ ይታያል። በዕርግጥ፣ የፅንስ አንደኛው አረዳድ ከዘር ፍሬዎች መዋሃድ ('ፈርቲላይዜሽን') ጋር አብሮ ይሄዳል፤ ሌላው ደግሞ ከዕርግዝና መጀመሪያ ከሆነው ከዘር ፍሬዎች መዋሃድ ተከትሎ እና የማህፀን ግድግዳ ላይ መጣበቅ ሲፈጠር ነው። ስለዚህ ነፍስ ከቁሳዊው አካል ጋር ትስስር የምትፈጥርበትን ጊዜ ለማወቅ አይቻል ይሆናል፣እንዲህ ያሉ ጥያቄዎችም ከመንፈሳዊ ዓለም ምሥጢሮች እና ከነፍስ ከራሷ ተፈጥሮ ጋር ስለሚያያዝ በሰው አስተሳሰብና ምርመራ ሳይፈታ ይችላል።"[3]**

1. የሰው ነፍስ ወደ ሕልውና የሚመጣው መቼ ነው? ________________________________

 ____________________________________________________________________

 ____________________________________________________________________

2. "ፅንስ" የሚለው ቃል ትክክለኛ ስነሕይወታዊ/ባዮሎጂካል ወቅትን ይገልፃል? ______________

____________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 3

በነፍስና በሰው አካል መካከል ያለው ግንኙነት ቁሳዊ አይደለም፤ ነፍስ ወደ ሰው አካል አትገባም ወይም አትወጣም እንዲሁም ቁሳዊ ስፍራ አትይዝም። ከአካል ጋር ያላት ትስስር ብርሃንን ከሚያንፀባርቀው መስታወት ጋር ይመሳሰላል። በመስታወቱ ውስጥ የሚታየው ብርሃን መስታወቱ ውስጥ አይደለም። በተመሳሳይ ነፍስ በአካል ውስጥ አይደለችም። አብዱል—ባሃ እንዲህ ያመላክተናል፣

> **"አመዛዛኝ ነፍስ፣ ወይም የሰው መንፈስ፣ በዚህ አካል ውስጥ ወርዳ አትኖርም ማለትም እሷ ውስጥ አትገባም፤ መውረድና መግባት የአካላት ባሕርያት ሲሆኑ፣ አመዛዛኝ ነፍስ ከዚህ በላይ የተቀደሰች ናት። ሲጀመር ነፍስ ወደዚህ አካል ፈፅሞ አልገባችም፣ በምትተውም ጊዜ ሌላ መኖሪያ ሥፍራ አትፈልግም። ይልቁንም የመንፈስ ከአካል ጋር ያለው ግንኙነት ልክ ይህ መብራት ከመስታወት ጋር እንዳለው ግንኙነት ነው። መስታወቱ ከተወለወለና እንከን ከሌለው፣ የመብራቱ ብርሃን እዚያ ውስጥ ይታያል፣ መስታወቱ ከተሰበረ ወይም በአቧራ ከተሸፈነ ደግሞ፣ ብርሃኑ ተሰውሮ ይቀራል።"[4]**

1. ከሥር ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች ባዶ ቦታዎቹን ሙሉ።

   ሀ. አመዛዛኝ ነፍስ፣ ወይም ______________________________በዚህ አካል ውስጥ ወርዳ አትኖርም ማለትም እሷ ውስጥ ________________________________ ።

   ለ. ________________________፣ወይም የሰው መንፈስ በዚህ አካል ውስጥ ወርዳ አትኖርም ማለትም እሷ ውስጥ አትገባም፤ መውረድና መግባት ______________________________ ሲሆኑ፣ አመዛዛኝ ነፍስ ______________________________________________________።

   ሐ. ሲጀመር ነፍስ ወደዚህ ________________________________________፣ በምትተወውም ጊዜ _____________________________________________________________ አትፈልግም።

   መ. የመንፈስ ከአካል ጋር ያለው ግንኙነት ልክ ________________________________________ እንዳለው ግንኙነት ነው።

   ሠ. መስታወቱ ከተወለወለና እንከን ከሌለው፣ ________________________________________ እዚያ ውስጥ ይታያል።

   ረ. መስታወቱ ከተሰበረ ወይም በአቧራ ከተሸፈነ፣ደግሞ ________________________________።

2. እስካሁን ባጠናነው ላይ በመመርኮዝ፣ የሚከተሉት እውነት መሆናቸውን ወስኑ:-

   ________ ነፍስ የቁሳዊ ዓለም አካል አይደለችም።
   ________ ነፍስ በአካል ውስጥ ናት።
   ________ አካል የነፍስ ባለቤት ነው።
   ________ ነፍስ አትሞትም።

________ የአንድ ግለሰብ የእርሱ ወይም የእርሷ መጀመሪያ የሚሆነው ነፍስ እራስዋን ከፅንስ ጋር ስታስተሳስር ነው።

________ ሕይወት የሚጀምረው ግለሰቡ ወደዚህ ዓለም ሲወለድ ነው።

________ የግለሰብ ቁሳዊ ሕይወት ከሞት በኋላ ይቀጥላል።

________ ሕይወት በየዕለቱ የሚፈጠርብንን ነገሮች ያካትታል።

3. በነፍስና በሰው አካል መካከል ያለውን ግንኙነት ለመግለፅ የብርሃንን ምስልና መስታወት ተጠቀሙ :- ________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

## ምዕራፍ 4

የሰው ልጅን በጋራ በሚመሠርቱት፣ በነፍስ እና በሰው አካል መካከል በጣም የተለየ ግንኙነት አለ። ይህ ግንኙነት የሚዘልቀው የሟች ሕይወትን ዕድሜ ያክል ብቻ ነው። በመካከላቸው ያለው ጥምረት ሲቋረጥ፣ እያንዳንዱ ወደ መጣበት ይመለሳል፤ የሰው አካል ወደ አፈር ዓለም ነፍስም ዕድገተዋን ወደምትቀጥልበት መንፈሳዊ የአምላክ ዓለማት። አብዱል—ባሃ ሲገልጽ፦

**"የሰው መንፈስ መጀመሪያ ሲኖረው መጨረሻ ግን የለውም:- ለዘለዓለም ይኖራል።"[5]**

ከንግግሮቹም በአንዱ፣ሲያብራራ፦

**"መንፈስ አካልን አይፈልግም፣ ነገር ግን አካል መንፈስ ያስፈልገዋል፣ ወይም መኖር አይችልም። ነፍስ ያለ አካል መኖር ትችላለች፣ ነገር ግን አካል ያለ ነፍስ ይሞታል።"[6]**

ሞግዚቱም ሲገልጽ፦

**"የሰው ነፍስን በተመለከተ፦ በባሃኢ ትምህርቶች መሠረት የሰው ነፍስ በሰው ፅንስ መፈጠር ይጀምራል፣ ከአካል ከተለየችም በኋላ ማደጓንና ማብቂያ በሌለው የህይወት ደረጃዎች ውስጥ ማለፏን ትቀጥላለች። ስለዚህ እድገቷ ወሰን አልባ ነው።"[7]**

1. ከላይ ያሉትን ጥቅሶች ታሳቢ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ:-

ሀ. አካል ነፍስ ያስፈልገዋል? ________________________________

ለ. ነፍስ አካል ያስፈልጋታል? ________________________________

ሐ. ስንሞት በሰው አካልና ነፍስ መካከል ባለው ግንኙነት ላይ ምን ይፈጠራል? ____________

________________________________________________

መ. ከሞት በኋላ ነፍስ ላይ ምን ይፈጠራል? ________________________

_______________________________________________________________________

_______________________________________________________________________

ሠ. የነፍስ ዕድገት ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል? _______________________________________

_______________________________________________________________________

_______________________________________________________________________

ረ. ሕይወት የሚያበቃው መቼ ነው? _______________________________________________

_______________________________________________________________________

_______________________________________________________________________

2. ከሚከተሉት የትኞቹ በእነዚህ ክፍሎች ካጠናነው ጋር አብረው የሚሄዱ እንደሆነ ወስኑ፦

________ ሞት ቅጣት ነው።
________ በሰው አካልና ነፍስ መካከል ያለው ግንኙነት የሚዘልቀው የሚች ሕይወትን ዕድሜ ያክል ብቻ ነው።
________ የሰው አካል ዘለዓለም ማደግ ይችላል።
________ ነፍስ ለዘለዓለም ታድጋለች።
________ ሞት የሕይወት መጨረሻ ነው።
________ አካሎቻችን ከሞት ሲነሱ የፍርድ ቀን ይሆናል።
________ በሞት ሰዓት፣ ነፍስ በፊት ከነበራት የተሻለ ነፃነት አላት።
________ ሕይወት በሞት ያበቃል።
________ ሞትን ልንፈራ ይገባል።
________ ምግብ፣ አልባሳት፣ ዕረፍት፣ እና መዝናናት ለነፍስ አስፈላጊ ናቸው።
________ አካል ኃይሏን ስለሚጠቀምባት ነፍስ ደካማ ትሆናለች።
________ ነፍስ በአካል ሕመም ወይም ድክመት ተፅዕኖ አይደርስባትም።
________ የሰው ልጅ ከሞት በኋላም ቁሳዊ ፍላጎት ይኖረዋል።

## ምዕራፍ 5

ነፍስ እንደ ቁሳዊ ነገሮች ቁሳዊ ስፍራ እንደማትይዝና በተፈጥሮ ሕግ መሠረት እንደማ ትንቀሳቀስ ተመልክተናል። ነፍስ በዓለም ውስጥ ተፅዕኖዋን የምታሳርፈው በአካል አማክይነት ነው፣ ነገር ግን ይህ ነፍስ ኃይሏን የምትገልፅበት ብቸኛ መንገድ አይደለም። ባሃኦላህ እንዲህ ይገልፃል፦

**"በእውነት እላለሁ፣ የሰው ነፍስ ከመውጣትና ከመግባት ሁሉ በላይ የላቀች ናት። የረጋች ነች፣ ሆኖም ትንሳፈፋለች፤ ትንቀሳቀሳለች፣ ሆኖም የረጋች ነች።"[8]**

አብዱል—ባሃም እንዲህ ይነግረናል፦

**"የሰው መንፈስ ተፅዕኖ እና አረዳድ ሁለት ዓይነት እንደሆነ እወቅ፤ ማለትም፣ የሰው መንፈስ ሁለት የተግባርና ግንዛቤ አቀራረብ አለው። አንደኛው አቀራረብ በአካላዊ መሣሪያዎችና የሰውነት ክፍሎች አማካይነት ነው። ስለዚህ በዓይን ያያል፣ በጆሮ ይሰማል፣ በምላስ ይናገራል። …**

***“ሌላው የመንፈስ ተፅዕኖ እና ተግባር አቀራረብ ያለ እነዚህ አካላዊ መሣሪያዎችና የአካል ክፍሎች ነው።”*** [9]

1. *የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ባዶ ቦታዎቹን ሙሉ።*

*ሀ. የሰው ነፍስ ከ______________________ና __________________ ሁሉ በላይ የላቀች ናች።*

*ለ. __________________________ ነች፣ ሆኖም ________________________________ነች ።*

*ሐ. __________________________ ነች፣ ሆኖም ________________________________ ነች።*

2. *ነፍስ በዚህ ዓለም ውስጥ ያላት አረዳድ እና የምታሳርፈውን ተፅዕኖ ሁለት መንገዶችን ግለጹ፦*

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

3. *ነፍስ ያለ አካል መሣሪያነት የምታሳርፈውን ተፅዕኖና ተግባር ምሳሌዎች ልትሰጡ ትችላላችሁ?*

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 6

*አሁን በቀደሙት ምዕራፎች ውይይት መነሻነት፣ ከባሃኦላህ ቅዱሳን ጽሑፎች የሚከተለውን ምንባብ አንብቡ፦*

> ***“የሰው ነፍስ ከአካል ወይም ከአዕምሮ ድክመቶች ሁሉ በላይ የላቀች፣ እንዲሁም ነፃ የሆነች መሆንዋን እወቅ። የታመመ ሰው የድክመት ምልክቶች የሚያሳየው በነፍሱና በአካሉ መካከል ጣልቃ በሚገቡ መሰናክሎች ምክንያት ነው፣የነፍስ የራሷ ሁኔታ ግን በማንኛውም የአካል ሕመም ወይም በሽታ ሳይለወጥ ይኖራል። የፋኖሱን ብርሃን አስቡ። ምንም እንኳ ውጫዊው ነገር ነፀብራቁን ቢጋርድ፣ ብርሃኑ ራሱ ግን ባልተቀነሰ ኃይል ማንፀባረቁን ይቀጥላል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የሰውን አካል የሚያሰቃየው እያንዳንዱ ህመም የነፍስን ተፈጥሮአዊ አቅሟንና ኃይሏን እንዳትገልጽ የሚከለክል መሰናክል ነው። ሆኖም፣ ከአካል በምትለይበት ጊዜ፣ ምንም በምድር የሚገኝ ኃይል በማይስተካከለው ሁኔታ ከፍተኛ የበላይነት ታሳያለች፤ የተለየ ተፅዕኖዋንም ትገልፃለች። እያንዳንዷ ንፁህ፣ እያንዳንዷ የጠራችና የተቀደሰች ነፍስ ታላቅ ኃይልን ትጎናፀፋለች፤ በከፍተኛ ሐሴትም ትፈነድቃለች።”*** [10]

1. *ነፍስ ከአካልና አዕምሮ ድክመቶች ተፅዕኖ ሳይደርስባት እንዴት እንደምትኖር፣ እና ከአካል ስትለይም ምን ግልፅ እንደሚሆን በራሳችሁ ቃላት ግለፁ።* ______________________________

2. ከቁሳዊ አካሎቻችን ሞት በኋላ ማንነታችንን ጠብቀን እንቀጥላለን?

## ምዕራፍ 7

ባሃኦላህ እንዲህ ይለናል፦

> **"አሁን ደግሞ ስለ ሰው ነፍስና ከሞት በኋላ መኖር መቀጠሏን ስለሚመለከተው ጥያቄህ። ነፍስ ከአካል ከተለየች በኋላ ፈጣሪዋ ዘንድ እስክትደርስ ድረስ፣ የዘመናትና የምዕተ ዓመታት መለዋወጥም ሆነ፣ እንዲሁም የዚህ ዓለም ለውጦችና አጋጣሚዎች በማይለውጣት አኳኋንና ሁኔታ ዕድገቷን የምትቀጥል መሆኑን በእውነት እወቅ። የአምላክ መንግሥት፣ ሉዓላዊነቱ፣ ገዥነቱና ሥልጣኑ እስካለ ድረስ ትኖራለች። የአምላክ ምልክቶችና ባሕርያትን ትገልፃለች፤ ፍቅር የተመላበት ደግነቱንና ቸርነቱንም ታሳያለች።"[11]**

1. ከአካላዊ ሞት በኋላ ነፍስ ዕድገቷን የምትቀጥለው ለምን ያህል ጊዜ ነው?

2. ነፍስ ወደ አምላክ ቅርበት የምታደርገውን ዘለዓለማዊ ጉዞ የምትቀጥለው በምን ሁኔታ ውስጥ ነው?

3. ነፍስ በዚያ ሁኔታ የምትገልፃቸው አንዳንድ መልካም ባሕርያትና ምልክቶች ምንድን ናቸው?

4. እስካሁን ባጠናናቸው ላይ በመመርኮዝ፣ የሚከተሉት እውነት መሆናቸውን ወስኑ:-

________ የአምላክ መንግሥት ለዘለዓለም ይኖራል።
________ ነፍስ የአምላክን ባሕርያት የመግለጽ ችሎታ አላት።
________ ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩት የምናደርገው ጸሎት ለነፍሳቸው ዕድገት አስተዋፅኦ አያደርግም።
________ ነፍስ መኖሯን ፈፅሞ አታቋርጥም።

## ምዕራፍ 8

ባሃኦላህ እንዲህ ያውጃል፦

**"እያንዳንዱ ሰሚ ጆሮ በንጽህናና ሳይበከል ከተጠበቀ፣በሁሉ ጊዜያትና ከሁሉ አቅጣጭ እነዚህን 'በእውነቱ፣እኛ የአምላክ ነን፣ ወደ እርሱም እንመለሳለን' የሚሉትን ቅዱሳን ቃላት የሚናገረውን ድምፅ እንደሚሰማ እወቅ። የሰው አካላዊ ሞትና የመመለሱ ምሥጢሮች አልተገለፁም፣አሁንም ግልፅ አልተደረጉም። ...**

**"ሞት ለእያንዳንዱ ዕርግጠኛ አማኝ በዕርግጥ ሕይወት የሆነውን ፅዋ ይሰጣል። ሐሴትን ያድላል፣ድስታንም አምጪ ነው። የዘለዓለማዊውን ሕይወት ስጦታ ያጎናፅፋል።**

**"ስለእነዚያ፣ ክብሩ ይስፋና፣ አንዱን እውነተኛ አምላክ ማወቅ ከሆነው፣ የሰውን ምድራዊ ሕይወት ፍሬ የቀመሱት፣ ከሞት በኋላ ያለው ሕይወታቸው እኛ ልንገልፀው የማንችለው ዓይነት ነው። የዚያ ዕውቀት ከአምላክ፣ከዓለማት ሁሉ ጌታ ጋር ብቻ ነው።"[12]**

**"የእርሱ ከሁሉ የበላይ የሆነው ልጅ ሆይ! እኔ ሞትን የድስታ መልዕክተኛ እንዲሆንልህ አድርጌልሃለሁ። ስለምን ታዝናለህ? ብርሃኑም ድምቀቱን እንዲያለብስህ አድርጌአለሁ። ለምን ራስህን ከዚያ ትጋርዳለህ?"[13]**

1. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች የትኞቹ እውነት ናቸው?

________ የሰው ልጅ ነፍስ የምትመጣው ከአምላክ ነው ወደ እርሱም ትመለሳለች።
________ ከሞት በኋላ ሕይወትን የተመለከተ እውቀት ሁሉ ከአምላክ ዘንድ ነው።
________ ዕርግጠኛ ለሆነ አማኝ፣ ሞት ሕይወት ነው።
________ ሞት ደስታን አምጪ ነው።
________ የሞት ምስጢሮች በሁሉም የታወቁ ናቸው።
________ የሕይወትን ፀጋዎች ዋጋ ልንሰጠው ይገባል ሆኖም ሞትን መፍራት የለብንም፣ሞት የደስታ መልዕክተኛ ነውና።
________ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት ማወቅ አስፈላጊያችን አይደለም።

2. እስካሁን ያጠናናቸውን ምዕራፎች ታሳቢ በማድረግ፣ ስለ ሕይወት፣ ሞት፣ አካልና ነፍስ አጠር ያለ አንቀጽ ፃፉ።

____________________________________________________________

____________________________________________________________

## ምዕራፍ 9

አብዱል—ባሃ ሲገልጽ፦

**“በሕይወቱ መጀመርያ ሰው ወደዚህ ዓለም ለመራመድ የሚያበቁትን ችሎታዎችና ብቃት ባዳበረበት ስፍራ በማህፀን ዓለም ነበር። ለዚህ ዓለም የሚያስፈልጉት ኃይሎች በዚያ ዓለም ተለገሱት። በዚህ ዓለም ውስጥ ዓይኖች አስፈለጉት፤ በማሕፀን ዓለም አገኛቸው። ጆሮዎች በዚህ ዓለም አስፈለጉት፣ በዚያ እያለ አገኛቸው። በዚህ ዓለም የሚያስፈልጉት ኃይሎች በሙሉ በማህፀን ዓለም እያለ ተለገሱት። በዚያኛው ዓለም ለዚህ ዓለም ዝግጁ ሆነ፣ ወደዚህ ዓለምም ሲገባ የሚያስፈልጉትን ኃይሎች ሁሉ እንዳሉት እና ለዚህ ሕይወት አስፈላጊ የሰውነት ክፍሎች ሁሉ በዚያ ዓለም እንዳገኘ ተመለከተ። ስለዚህ በዚህ ዓለምም ለወዲያኛው ዓለም መዘጋጀት ይኖርበታል። በአምላክ መንግሥት ዓለም የሚያስፈልገውን እዚህ እያለ ማግኘትና ማዘጋጀት ይገባዋል። ልክ ለዚህ ዓለም አስፈላጊ የሆኑትን ኃይሎች በማህፀን ዓለም እያለ እንዳገኘ ሁሉ፣ በተመሳሳይ በመንግሥተ ሰማያዊው ዓለም የሚፈልጋቸውን፣ ማለትም መለኮታዊ ኃይሎችን በዚህ ዓለም ማግኘት አለበት።”[14]**

1. የሚከተሉት እውነት መሆናቸውን ወይም አለመሆናቸውን ይወስኑ:-

________ ለዚህ ዓለም የሚያስፈልጉ ኃይሎች ሁሉ የሚገኙት በማህፀን ዓለም ውስጥ ነው።

________ ራስን ለቀጣዩ ዓለም ሕይወት ማዘጋጀት አስፈላጊ አይደለም::

________ በዚያኛው መንግሥተ ሰማያዊ ዓለም የምንፈልገውን ማግኘት ያለብን እዚያው ነው::

________ የዚህ ሕይወት ዓላማ ለቀጣዩ ዓለም የሚያስፈልጉ ኃይሎችን ለመቀዳጀት ነው::

________ እውነተኛ ሕይወት የሚጀምረው አንድ ሰው ሲሞትና ወደ መለኮታዊው መንግሥት ሲገዝ ነው::

________ እውነተኛ ሕይወት በዚህ ዓለም ይጀምራል ከአካላዊ ሞት በኋላም ይቀጥላል::

2. የሰው ልጅ በማህፀን ዓለም የሚያገኛቸው አንዳንድ ችሎታዎች ምንድን ናቸው?____________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

3. ከሞት በኋላ ላለው ሕይወት እዚህ ሊገኙ የሚገቡ አንዳንድ ሥጦታዎች ምንድን ናቸው?______

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

## ምዕራፍ 10

ባሃኦላህ እንዲህ ያውጃል፦

**“በዚህ ቀን የሰው ሙሉ ተግባር ያንን አምላክ የሚያፈስለትን የፀጋ ጎርፍ ድርሻ ለመቀዳጀት መብቃት ነው:: ስለዚህ ማንም ስለመቀበያው ትልቅነት ውይም ትንሽነት አያስብ:: የአንዳንዱ ድርሻ የአንድ እፍኝ ያህል ይሆናል፤ የሌሎች ድርሻ አንድ ፍንጃል፤ የሌሎች ደግሞ የአንድ ጋሎን ልኬት ያህል እንኳን ይሆናል::”[15]**

1. ከላይ ባለው ጥቅስ ላይ በመመርኮዝ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ:-

ሀ. በዚህ ቀን የእያንዳንዱ ግለሰብ ተግባር ምንድን ነው?________________________

________________________________________

ለ. ከአምላክ የተቀበላችሁት አንዳንድ ቡራኬዎች ምን ምን ናቸው? ________________

________________________________________

________________________________________

ሐ. በላይኛው ጥቅስ ውስጥ “መቀበያ” የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል? ______________

________________________________________

________________________________________

መ. ስለተለገሰን ችሎታ “ትልቅነት ወይም ትንሽነት” ከግምት ውስጥ ማስገባት የማይገባን ለምንድን ነው? ______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ሠ. የአምላክ ፀጋ ድርሻችንን ከመቀበል የሚገቱን አንዳንድ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? ______

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

2. ከሚከተሉት የትኞቹ እውነት ናቸው?

________ የችሎታችን “ትልቅነት ወይም ትንሽነት” ምን ያህል ኀበዝ እንደሆንን ያመለክታል።

________ አምላክን ለማገልገል፣ ድክመታችንን ዘንግተን መላ እምነታችንን በእርሱ ላይ ማድረግ አለብን።

________ አምላክ የቸረንን ችሎታዎች በዚህ ዓለም ካላድበርን፣ በቀጣዩ ዓለም ውስጥ ስንደርስ ነፍሳችን ደካማ ትሆናለች።

## ምዕራፍ 11

ባሃኦላህ እንዲህ ይገልፃል፦

**“የነፍስን ተፈጥሮ በሚመለከት ጥያቄ ጠይቀኸኛል። በእውነት፣ ነፍስ እውንነቷን በትምህርት እጅግ በጣም የላቁት ሰዎች ሊገነዘቧት የተሳናቸው፣ ምሥጢሯንም ምንም አዕምሮ፣ ምንም ያህል አስተዋይ ቢሆንም፣ሊፈታው ተስፋ ለማድረግ ከቶ የማይችል፣ የአምላክ ምልክት፣ መንግሥተ ሰማያዊ ዕንቁ መሆንዋን እወቅ። ከተፈጠሩትም ነገሮች መካከል የፈጣሪዋን ፍፁምነት ለማወጅ፣ ክብሩን አውቃ ለመቀበል፣በእውነቱም ላይ ለመጣበቅ፣ በማምለክም በፊቱ ለመንበርከክ የመጀመሪያ ናት።”[16]**

1. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ባዶ ቦታዎች ሙሉ።

ሀ. ነፍስ የአምላክ ______________________ ናት።

ለ. ነፍስ ____________________ በትምህርት እጅግ በጣም የላቁት ሰዎች ሊገነዘቧት የተሳናቸው፣______________ምንም አዕምሮ፣ ምንም ያህል አስተዋይ ቢሆንም፣ ____________________ተስፋ ለማድረግ ከቶ የማይችል፣ የአምላክ ምልክት፣ ______________________________________ መሆንዋን እወቅ።

ሐ. ነፍስ ከ ______________________________ የ______________

______________ ለማወጅ ______________________________ናት።

መ. ነፍስ የአምላክን ክብር ______________________________ የመጀመሪያ ናት።

ሠ. ነፍስ በአምላክ እውነት ላይ ______________________________ የመጀመሪያ ናት።

ረ. ነፍስ በአምላክ በማምለክ በፊቱ ______________________________ የመጀመሪያ ናት።

2. ከሚከተሉት የትኞቹ እውነት ናቸው?

________ "መፍታት" ማለት መለየት ማለት ነው።
________ ከተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ፣ አምላክን ለመገንዘንብ የመጀመሪያው የሰው አዕምሮ ነው።
________ "አስተዋይ" ማለት ስል ማለት ነው።
________ የተማረ ሰው የነፍስን ምሥጢር ይገነዘባል።
________ የአምላክን ፍፁምነት ታላላቅ ፈላስፎች ብቻ ሊገልፁት ይችላሉ።
________ ልንገነዘበው ፈፅሞ ስለማንችል ስለነፍስ ማሰብ አስፈላጊ አይደለም።

## ምዕራፍ 12

ባሃኦላህ እንዲህ ያውጃል፦

**"እናንት ልክ በኃያል ክንፎቿ ሙሉ ኃይል፣ በፍፁምና ሐሴት በተመላበት ልበሙሉነት፤ በሰማያት ሰፊ ስፋት ውስጥ ትበር እንደንበረችዋና፣ በኋላም ረሃብዋን ለማስታገስ ከበታች ወዳለው ምድር ውሃና አፈር በጉጉት ተመልሳ፣ በምኞቷ መረብ ተጠምዳ፣ ወደ መጣችበት ዓለማት እንደገና በረራዋን ለመቀጠል ኃይል አልባ ሆና ራሷን እንዳገኘችው ወፍ ናችሁ። እስከዚያ ድረስ በሰማያት ትኖር የነበረችው ያቺ ወፍ፣ በጨቀዩ ክንፎችዋ ላይ የተጫነውን ክብደት ለማራገፍ ኃይል አልባ ሆና አሁን በትቢያ ላይ መኖሪያ ስፍራዋን ለመፈለግ ተገድዳለች። ስለዚህ፣ አገልጋዮቼ ሆይ፣ በመለኮታዊ ዕውቀቱ ሰማያት ውስጥ ከመብረር እንዳትገቱ፣ ክንፎቻችሁን በአመፀኝነትና በከንቱ ምኞቶች አፈር አትለውሱ፣ በቅናትና በጥላቻ አቧራም እንዲበከሉ አታድርጓቸው።"[17]**

1. ከሥር ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሟሉ።

ሀ. በዚህ ጥቅስ ባሃኦላህ የሚጠቅሳት ወፍ ______________________________ናት።
ለ. ይህች ወፍ የ ______________________________ ነዋሪ ናት።
ሐ. ክንፎችዋ ስለጨቀዩ፣ወፏ በ ______________________________ ላይ መኖሪያ ስፍራዋን ለመፈለግ ተገዳለች።

2. አሁን የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ:-

ሀ. የነፍስ "ክንፎች"እንዴት "የጨቀዩ" ይሆናሉ?______________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ለ. ልክ እንደ “ምድር ውሃና አፈር” በነፍስ ክንፎች ላይ የተጫኑ አንዳንድ ክብደቶች ምንድን ናቸው? ____________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ሐ. ወደ መለኮታዊ መንግሥተ ሰማያት ከመውጣት ሊያግዱን የሚችሉ አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?_____________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

መ. ነፍስ መንግሥተ ሰማያዊ መኖሪያዋን ለምን በዚህ ምድር አቧራ ትለውጣለች? _________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

3. የሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች እውነት መሆናቸውን ወስኑ:-

________ ዓለማዊ ቁርኝት መንፈሳዊ ዕድገታችንን ይገታሉ::

________ አመፀኛነታችንና ከንቱ ምኞታችን በመለኮታዊ እውቀት መንግሥተ ሰማያት ከመብረር ያግዱናል::

________ ቅናትና ጥላቻ የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ባሕርያት በመሆናቸው ለነፍስ ሸክም አይሆኑም::

________ ከዚህ ዓለም ነገሮች ራሳችንን በማላቀቅ በሰማያት ስፋት ውስጥ እንዳንበር ከሚያግዱን ሸክሞች እራሳችንን ነፃ ማውጣት እንችላለን::

________ የነፍስ መኖሪያ በዚህ ዓለም ውስጥ ነው::

## ምዕራፍ 13

ባሃኦላህ እንዲህ ይላል፦

**“ዓለምን እንዲሁም በውስጧ የሚኖሩትንና የሚንቀሳቀሱትን ከፈጠረ በኋላ፣ እርሱ፣ በማይገታውና በሉዓላዊ ፈቃዱ ቀጥተኛ ተልዕኮ፣ እንደ መላው ፍጥረት አንቀሳቃሽ ኃይልና ቀዳሚ ዓላማ መንስዔ መወሰድ ያለበትን ችሎታ፣ እርሱን የማወቅና የማፍቀርን ልዩ ክብርና ችሎታ በሰው ላይ ለማጎናጸፍ መረጠ:: ... እርሱ በእያንዳንዱና በሁሉም የተፈጠረ ነገር ውስጣዊ እውነታ ላይ ከስሞቹ የአንዱን ብርሃን ፈነጠቀበት፣ ከባሕርያቱም የአንዱን ክብር**

**ተቀባይ አደረገው። በሰው እውነታ ላይ ግን የእርሱን ስሞችና የባሕርያቱን ሁሉ ብርሃን አበራበት፣ የገዛ ራሱን መንፀባረቂያ መስታወት አደረገው። ከተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ እርሱ ብቻ ለዚህ ዓይነቱ ችሮታ፣ ዘላቂ ፀጋ ተመረጠ።”[18]**

1. ከሥር ያሉትን ባዶ ቦታዎች ሙሉ።

ሀ. አምላክ ______________________________ ልዩ ክብርና ችሎታ በሰው ላይ ለማጎናጸፍ መረጠ።

ለ. እርሱ ____________________ና ____________________የተፈጠረ ነገር ውስጣዊ እውነታ ላይ ____________________ብርሃን ፈነጠቀበት፣ ____________________ ____________________ ክብር ተቀባይ አደረገው።

ሐ. በሰው እውነታ ላይ ግን ______________________________ ብርሃን አበራበት፣____________________መንፀባረቂያ መስታወት አደረገው።

2. አሁን የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ:-

ሀ. አንዳንድ የአምላክን ባሕርያት ለመጥቀስ ትችላላችሁ? ____________________

______________________________

______________________________

______________________________

ለ. የሰው ነፍስ ልንታንፀባርቅ የምትችለው አንዳንድ የአምላክ ባሕርያት ምንድን ናቸው?______

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

ሐ. እነዚህ ባሕርያት እንዴት ሊገለፁ ይችላሉ?____________________

______________________________

______________________________

______________________________

መ. የሰው ልጅ የተመረጠው ለምን ዓይነት ልዩ ችሮታ ነው?____________________

______________________________

______________________________

______________________________

3. ከሚከተሉት የትኞቹ እውነት ናቸው?

________ የሰው ልጅ ከተቀሩት ፍጥረታት የተለየ አይደለም።
________ አምላክን የማወቅና የማፍቀር ችሎታ የመላው ፍጥረት አንቀሳቃሽ ኃይልና ቀዳሚ ዓላማ መንስዔ ነው።
________ የተፈጠሩት ነገሮች ሁሉ ውስጣዊ እውነታ ከአምላክ ባሕርያት አንዱን ተቀባይ ነው።
________ የሰው ነፍስ የአምላክን ባሕርያት በሙሉ ማንፀባረቅ ትችላለች።

## ምዕራፍ 14

ባሃኦላህ እንዲህ ይነግረናል፦

**“ልክ ነበልባሉ በሻማ ውስጥ እንደተደበቀና የብርሃኑም ጨረር ባልተገለፀ መልኩ በፋኖስ ውስጥ መኖሩ እንደሚታወቅ ሁሉ፣ የመለኮታዊ ልግስና የቀን ኮከብና የመንግሥተ ሰማያዊ መርሆ ምንጭ፣ የሰውን እውነታ ያጎናፀፉት እነዚህ ኃይሎችም፣ ገና ባልተገለጸ ሁኔታ በሰው ውስጥ ተደብቀው ይገኛሉ። የፀሐይ ብርሃን መስታወቱን በሸፈነው አቧራና ቆሻሻ ስር ሊደበቅ እንደሚችል ሁሉ፣ የእነዚህ ኃይሎች ብርሃንም በዓለማዊ ምኞቶች ሊጋረድ ይችላል። ሻማም ሆነ ፋኖስ ምንም ዕርዳታ ሳይደረግላቸው በራሳቸው ጥረት ሊበሩ እንደማይችሉ፣ እንዲሁም መስታወት ራሱን ከአቧራ ንጹህ ለማድረግ አይቻለውም። እሳቱ እስኪቀጣጠል ድረስ ፋኖስ ሊበራ ከቶ እንደማይችል፣ አቧራውም ከላዩ ካልተጠረገ የመስታወቱ ገፅ የፀሐይን መልክ ሊያሳይና ብርሃኗንና ግርማዋን ሊያንፀባርቅ ፈፅሞ እንደማይችል ግልፅና የተረጋገጠ ነው።”[19]**

1. “ገና ባልተገለጸ ሁኔታ የተደበቀ” ማለት ምን ማለት ነው? ________________________________

________________________________________________

2. በሰው ነፍስ ውስጥ ገና ባልተገለጸ ሁኔታ የተደበቁ አንዳንድ ኃይሎች ምንድን ናቸው? ___

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

3. ፋኖስ ምን ዕምቅ ኃይል አለው? ________________________________________

________________________________________________

4. መስታወት ምን እምቅ ኃይል አለው?________________________________________

________________________________________________

5. ፋኖሱ ብርሃን መስጠት እንዲችል ምን ማድረግ ይኖርባችኋል? __________________________

________________________________________________

________________________________________________

6. መስታወቱ ብርሃን ማንፀባረቅ እንዲችል ምን ማድረግ ይኖርባችኋል? ____________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

7. ፋኖሱና መስታወቱ ዕምቅ ኃይላቸውን በራሳቸው መግለጽ ይችላሉ? ____________________

_______________________________________________________________

8. እንዚህን ሁለት ምሳሌዎች ከሰው ነፍስ ሁኔታ ጋር እንዴት ልናዛምድ እንችላለን?___________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

9. የሰው ነፍስ ዕምቅ ኃይሏን እንድትገልጽ የሚያስችላት ማን ነው?________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

## ምዕራፍ 15

ባሃኦላህ እንዲህ ይገልፃል፦

***“የቀናት ቀደምቱን ሕያው የማወቅ በር ምን ጊዜም በሰዎች ፊት ላይ ዝግ ነበረ፣ ለወደፊትም ለዘላለም ዝግ መሆኑ ይቀጥላል። የማንም ሰው የመረዳት ኃይል ወደቅዱስ መንበሩ የመግባት ዕድል ምንጊዜም ሊያገኝ አይችልም። ሆኖም፣ የምህረቱ ስጦታ ምልክትና የፍቅራዊ ደግነቱ ማስረጃ ይሆን ዘንድ፣ የእርሱ መለኮታዊ መርሆ የቀን ከዋክብት፣ የመለኮታዊ አንድነቱን ምልክቶች ለሰዎች ገልጿል፤ እነዚህንም ቅዱሳን ሕያዊያን ማወቁ እርሱን ከማወቅ ጋር አንድ ዓይነት እንደሆነ ደንግጓል። እነርሱን ያወቀ አምላክን አውቋል። ጥሪያቸውንም ያዳመጠ የአምላክን ድምፅ ሰምቷል፤ የግልጸታቸውንም እውነተኝነት የመሰከረ፣ የአምላክን የራሱን እውነተኝነት መስክሯል። ከእነርሱ ፊቱን ያዞረ፣ ከአምላክ ፊቱን አዙሯል፤ በእነርሱም ያላመነ፣ በአምላክ ማመኑን ክዷል። እነርሱ እያንዳንዳቸው ይህን ዓለም ከላይኞቹ አለማት ጋር የሚያገናኝ የአምላክ ጎዳና፣በምድርና በሰማይ መንግሥታት ለሚገኝ ለእያንዳንዱም የእርሱ እውነት መለኪያ ነው። እነርሱ በሰዎች መካከል የአምላክ ክስተቶች፣የእውነቱ ማረጋገጫዎችና የእርሱ ክብር ምልክቶች ናቸው።”***[20]

1. የላይኛውን ጥቅስ ታሳቢ በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ:-

ሀ. አምላክን በቀጥታ ለማወቅ ይቻለናልን?__________________________________

_______________________________________________________________

ለ. ታዲያ፣ አምላክን እንዴት ልናውቅ እንችላለን?________________________________

__________________________________________________________________

ሐ. አንዳንድ የመለኮታዊ መርሆ የቀን ከዋክብትን ስም መጥቀስ ትችላላችሁ?__________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

መ. የአምላክ ግልፀቶችን ድምፅ ያዳመጡ የማንን ድምፅ ሰምተዋል? _______________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

ሠ. የአምላክ ግልፀቶችን ጥሪ ቸል ስንል ፊታችንን ከማን እያዞርን ነው?______________

__________________________________________________________________

2. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሟሉ፡፡

ሀ. የቀናት ቀደምቱን ሕያው የማወቅ በር ምን ጊዜም ___________________________
_____________________________፣ለወደፊትም ለዘላለም ዝግ መሆኑ ይቀጥላል፡፡

ለ. የማንም ሰው የመረዳት ኃይል ______________________________________
የመግባት ዕድል ምንጊዜም ሊያገኝ አይችልም፡፡

ሐ. አምላክ ___________________________________ምልክትና _____________
_______________________________ማስረጃ ይሆን ዘንድ የእርሱን ግልፀቶች ላከ፡፡

መ. የአምላክ ግልፀቶች ዕውቀት ___________________________________________
ጋር አንድ ዓይነት ነው፡፡

ሠ. እነርሱን ያወቀ _____________________________________________________፡፡

ረ. ጥሪያቸውንም ያዳመጠ _______________________________________________ ፡፡

ሰ. እነርሱ እያንዳንዳቸው ______________________________________________
____________________________ የአምላክ ጎዳና____________________________
__________________________________________________________________
__________________________________________________________________
__________________________________________________________________
________________________________________________________________፡፡

3. ከሚከተሉት የትኞቹ እውነት ናቸው?

________ በመንፈስ ልናድግ የምንችለው በራሳችን ጥረት አማካይነት ብቻ ነው፡፡

________ አምላክ አዕምሮ ሰጥቶናል፣ ለዕድገታችንም በቂ ነው።

________ የአምላክ ግልፀትን በማወቅ በመንፈስ እናድጋለን እና ተጨማሪ ጥረት ማድረግ አይኖርብንም።

________ የአምላክ ግልፀትን በማወቅ እና በእርሱ ትምህርቶች መሠረት ለመኖር በመጣር በመንፈስ ልናድግ እንችላለን።

________ አምላክን በቀጥታ ልናውቀው እንችላለን።

________ የሰው ልጅ እንደ አምላክ ሊሆን ይችላል።

________ አምላክ ከሰው ግንዛቤ በላይ ከፍ ያለ ነው።

________ የአምላክ ግልፀትን ቃላት ስናዳምጥ፣ የአምላክን ድምፅ እያዳመጥን ነው።

## ምዕራፍ 16

ባሃኦላህ እንዲህ ያውጃል፦

**"የአምላክ ነቢያትና መልዕክተኞች የተላኩበት ዋና ዓላማ የሰው ዘርን ወደ ቀጥተኛ የእውነት መንገድ ለመምራት ነው። የግልፀታቸው ዓላማ ማጠንጠኛ፣ ሁሉም ሰዎች በሞታቸው ሰዓት፣ በላቀ ንፅህናና ቅድስና እንዲሁም በፍፁም መላቀቅ ወደ እጅግ በጣም ከፍተኛው ዙፋን ማረግ ይችሉ ዘንድ ለማስተማር ነው።"**[21]

እርሱ በሌላ ምንባብም እንዲህ ይላል፦

**"ሰው የላቀ ስጦታ ያለው ፍጡር ነው። ተገቢ ትምህርት አለማግኘቱ ግን፣ በተፈጥሮ ያለውን ችሎታ ነፍጎታል። ከአምላክ አፍ በወጣ አንድ ቃል ወደ መኖር ተጠራ፤ በአንድ ተጨማሪ ቃል የትምህርቱን ምንጭ ወደማወቅ ተመራ፤ በአንድ ሌላ ቃል ደግሞ ደረጃውና ዕጣፈንታው ተከበሩ። ታላቁ ሕያው እንዲህ ይላል፦ ሰውን ዋጋው ከግምት በላይ የሆኑ የበለፀጉ ዕንቁዎች እንዳለበት የማዕድን ስፍራ ቁጠሩት። ሐብቱን እንዲገለጽ ሊያደርገው የሚችለው፣ የሰውንም ዘር ከዚያ ተጣቃሚ የሚያደርገው ትምህርት ብቻ ነው። ማንም ሰው ከዚያ ከአምላክ ቅዱስ ፈቃድ ሰማይ የተላኩት ቅዱሳት መጻሕፍት የገለፁትን ቢያሰላስል፣ ዓላማቸው ሰዎች ሁሉ እንደ አንድ ነፍስ እንዲቆጠሩ ለማድረግ፣ በዚህም 'መንግሥት የአምላክ ይሆናል'፤የሚሉትን ቃላት የያዘው ማኅተም በእያንዳንዱ ልብ ላይ እንዲታተምና፣ የመለኮታዊ በረከት፣ የፀጋና የምህረት ብርሃን የሰውን ዘር ሁሉ እንዲያለብስ፣ዓላማቸው እንደሆነ ወዲያውኑ ይገነዘባል።"**[22]

1. የአምላክ ነቢያትና መልዕክተኞች የተላኩት ለምን ዓላማ ነው?________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

2. የግልፀታቸው ዓላማ ማጠንጠኛ ምንድን ነው?________________________________

________________________________________________________________

3. “የላቀ ስጦታ ያለው” ማለት ምን ማለት ነው?

4. ተገቢ ትምህርት ያለማግኘት ውጤቱ ምንድን ነው?

5. ተገቢ ትምህርት ምን ውጤት ሊያመጣ ይችላል?

6. የትምህርታችን ምንጭ ምንድን ነው?

7. ዕጣ-ፈንታችን ምንድን ነው?

8. ትምህርት የሚገልፃቸው አንዳንድ ዕንቁዎች ምንድን ናቸው?

9. በቅዱሳን ጽሑፎች ላይ ስናሰላስል ወዲያው የምንገነዘበው ምንድን ነው?

## ምዕራፍ 17

ባሃኦላህ እንዲህ ይገልፃል፦

**"ከዚህም በላይ፣ ነፍስ ከአካል ከተለየች በኋላ ስለሚኖራት ሁኔታ በተመለከተ ጠይቀኸኛል። የሰው ነፍስ በአምላክ መንገዶች ከተጓዘች፣ እርሷ፣ በዕርግጥ ወደ ተወዳጁ ክብር የምትመለስና የምትሰበሰብ መሆኗን በእውነት እወቅ። በአምላክ ትክክለኝነት! ብዕር ሊፅፈው፣ ወይም አንደበት ሊገልፀው የማይችለውን ደረጃ ትቀዳጃለች። ለአምላክ እምነት ታማኝ ሆና የቆየችና በእርሱ መንገድ ሳታወላውል ፀንታ የቆመች ነፍስ፣ ከዕርገትዋ በኋላ፣ የሚኖራት ኃይል ከፍ ያለ ከመሆኑ የተነሳ ኃያሉ አምላክ የፈጠራቸው ዓለማት ሁሉ በእርስዋ አማካይነት ሊጠቀሙ ይችላሉ።"[23]**

1. የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች አሟሉ:-

ሀ. የሰው ነፍስ በአምላክ መንገዶች ከተጓዘች፣ በዕርግጥ____________________

____________________________________________።

ለ. ____________________________________________

__________________________________ደረጃ ትቀዳጃለች።

ሐ. ለ ________________________________ ሆና የቆየችና

______________________ሳታወላውል________________

ነፍስ፣ ________________ በኋላ፣ የሚኖራት ________________ ከፍ

ያለ ከመሆኑ የተነሳ ______________________________ዓለማት

ሁሉ በእርስዋ አማካይነት ____________________ ይችላሉ።

## ምዕራፍ 18

ባሃኦላህ እንዲህ ይነግረናል፦

**"ከአካል በምትለይበት ሰዓት፣ ከዓለም ሕዝቦች ከንቱ አስተሳሰቦች ነፃ የሆነች ነፍስ የተባረከች ነች። እንደዚህ ያለች ነፍስ የምትኖረውና የምትንቀሳቀሰው በፈጣሪዋ ፈቃድ መሠረት ነው፣ ከሁሉ በላይ እጅግ በጣም ከፍተኛው ገነትም ትገባለች። የመንግሥተ ሰማይ ድንግሎች፣የእጅግ በጣም ከፍተኛው ቤት ነዋሪዎች ያጅቧታል፤ እንዲሁም የአምላክ ነቢያትና የእርሱ ምርጦች ጓደኝነቷን ይሻሉ። ያቺ ነፍስ ከእነርሱ ጋር በነፃነት ታወጋለች፣ የዓለማት ሁሉ ጌታ በሆነው አምላክ መንገድ እንድትቋቋም የተደረገችውንም ታጫውታቸዋለች።"[24]**

**"እርሱ ለኃጢአተኛው ይቅርታ ማድረግ አለበት፤ በዝቅተኛነቱም ሁኔታ ሳቢያ ፍፁም መናቅ የለበትም፣ የራሱ መጨረሻ ምን እንደሚሆን ማንም አያውቅምና። ኃጢአተኛ በሞቱ ሰዓት የእምነት ሕልውና የተቀዳጀው፣ ሞት አልባውን ጠበል በመጨለጥም፣ ወደ ሰማይ ሠራዊት በረራውን ያደረገውስንት ጊዜ ነው! እንዲሁም ፅኑ አማኝ በነፍሱ ማረግያ**

**ሰዓት፣ በጣም ከመለወጡ የተነሳ የመጨረሻ አዘቅት እሳት ውስጥ የወደቀው ስንት ጊዜ ነው::”[25]**

1. ነፍሳችን ከአካል ስትለይ በምን ሁኔታ ልትሆን ይገባል?________________________

2. አንዳንድ ከንቱ አስተሳሰቦች ምንድን ናቸው?________________________

3. ከከንቱ አስተሳሰቦች የተቀደሰች ነፍስ ከሞት በኂላ በምን ዓይነት ሁኔታ ነው የምትኖረውና የምትንቀሳቀሰው? ________________________

4. እንዲህ ላለችው ነፍስ ጓደኛ የሚሆኗት እነማን ናቸው?________________________

5. እንዲህ ያለችው ነፍስ ከአምላክ ነቢያትና ከእርሱ ምርጦች ጋር ማውጋት ትችላለች?______

6. ምድራዊ ሕይወታችን እንዴትና መቼ እንደሚያበቃ አስቀድመን እናውቃለን?____________

7. ለእኛ የታደለውን ዘለዓለማዊ ሕይወት ለመቀዳጀት አሁን ምን ማድረግ እንችላለን?_______

## ምዕራፍ 19

አብዱል—ባሃ ሲገልጽ፦

**"የሰው መንፈስ ይህን ቁሳዊ ማዕቀፍ ካራገፈ በኋላ፣ ለዘለዓለም ስለሚኖር፣ ልክ ሕይወት እንዳላቸው ነገሮች ሁሉ፣ ያለጥርጥር ማደግ ስለምትችል፣ አንድ ሰውም በሞት ለተለየች ነፍስ ዕመርታ፣ ይቅርታ እንዲደረግላት፣ ወይም የመለኮታዊ ስጦታዎች፣ ፀጋዎች፣ እና ሞገስ ተቀባይ እንድትሆን ጸሎት ማድረግ ይችላል። ለዚህም ነው በባሃኦላህ ጸሎቶች ውስጥ፣ ወደዚያኛው ዓለም ላለፉት ነፍሳት የአምላክን ይቅርታና የኃጢአት ሥረየት የምንማፀነው። ከዚያም በላይ፣ልክ ሰዎች በዚህ ዓለም አምላክ እንደሚያስፈልጋቸው፣ በቀጣዩም እርሱ ያስፈልጋቸዋል። በዚህም ዓለምም ሆነ በሚመጣው ፍጡራን ምንጊዜም ጥገኞች ናቸው፣ አምላክ ግን ምንጊዜም ከእነርሱ ፈፅሞ ነፃ ነው።"[26]**

በሞት ለተለዩ ነፍሳት መፀለይ ያለብን ለምንድን ነው?

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 20

አብዱል—ባሃ ሲጽፍ፦

**"የሰው ነፍስ ከዚህ አላፊ ቁልል አቧራ ተላቃ ስትበርና ወደ አምላክ ዓለማት ከፍ ስትል፣ ግርዶሾች ይወገዳሉ፣ እውነታዎችም ገሃድ ይወጣሉ፣ በፊት ያልታወቁ ነግሮች ሁሉ ግልፅ ይሆናሉ፣ የተደበቁ እውነታዎችም ይታወቃሉ።**

**"ሰው በማህፀን ዓለም ውስጥ፣የማይሰማ ጆሮና የማያይ ዓይን፣ እንዲሁም የማይናገር ምላስ፤ ከማንኛውም ዓይነት መረዳት የተነፈገ እንደነበረ አስተውሉ። ነገር ግን ከዚያ ጨለማ ዓለም ወጥቶ ወደዚህ የብርሃን ዓለም ሲገባ፣ ዓይኑ አየ፣ ጆሮው ሰማ፣ ምላሱም ተናገረ። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ከዚህ ሟች ሥፍራ ወደ አምላክ መንግሥተ ሰማያት እንዴ ካመራ፤ በመንፈስ ይወለዳል፤ ከዚያም የመረዳት ዓይኑ ይከፈታል፣ የነፍሱ ጆሮ ያዳምጣል፣ በፊት የማያውቃቸውም እውነታዎች ሁሉ ግልፅና ጥርት ያሉ ይሆናሉ።"[27]**

1. ከሥር ያሉትን ባዶ ቦታዎች ሙሉ።

ሀ. የሰው ነፍስ ይህን ዓለም ስትተው፣ ከዚያ

__ ግርዶሾች ______________________________፣

__ እውነታዎችም____________________________________፣

__ እነዲሁም በፊት ያልታወቁ ነግሮች ሁሉ ________________________________፣

__ የተደበቁ እውነታዎችም _____________________________________________::

ለ. እኛ _________________________ ዓለም ውስጥ፣የ________________________ጆሮ

___________________________ዓይን፣ እንዲሁም______________________________

ምላስ ነበረን::

ሐ. ወደዚህ ዓለም ስንወለድ፤ ዓይናችን ________________፣ ጆሮአችን _______________፣

ምላሳችንም __________________ ::

መ. በተመሳሳይ ሁኔታ፣ከዚህ ሟች ሥፍራ ወደ አምላክ መንግሥተ ሰማያት አንዴ ካመራን፣ በ_________________________________________::

ሠ. ከዚያም የ_________________ ዓይናችን ____________________________፣

የ_________________ ጆሮ ___________________________፣ በፊት የማናውቃቸውም

____________________ሁሉ _________________ና ______________ያሉ ይሆናሉ::

2. የሚከተሉት ዓረፍተ ነግሮች እውነት መሆናቸውን ወስኑ:-

________በማህፀን ዓለም ውስጥ እያለን፣ ስለዚህ ዓለም እናውቃለን::

________ ከሞት በኋላ ያለ ሁኔታችን በዚህ ሕይወታችን ውስጥ የተሸሸገ እውነታ ነው::

________ ከሞት በኋላ አዳዲስ አድማሶች በሙሉ ከፊታችን ይገለጣሉ::

________ ስንሞት፣ እንደገና ለመወለድ ወደዚህ ዓለም እንመለሳለን::

## ምዕራፍ 21

ባሃኦላህ እንዲህ ይገልፃል፦

**"አሁን ደግሞ የሰዎችን ነፍሶች ከአካል ከተለዩ በኋላ እርስ በርሳቸው መተዋወቃቸውን መቀጠል አለመቀጠላቸውን ስለሚመለከተው ጥያቄህ:: ወደ ቀይዋ መርከብ ውስጥ የገቡና በዚያ የሚኖሩ የባሃ ሕዝብ ነፍሶች እርስ በርሳቸው ይወዳጃሉ፣ የጠበቀ ግንኙነትም ያደርጋሉ፣ በአኗኗራቸው፣ በፍላጎቶቻቸው፣ በዓላማዎቻቸውና በጥረታቸው በጣም ተቀራርበው ከመኖራቸው የተነሳ ልክ እንደ አንድ ነፍስ ይሆናሉ:: እነርሱ በዕርግጥ እነዚያ በቂ ዕውቀት ያላቸው፣ አስተዋይ አመለካከት ያላቸው፣ መረዳትንም የተለገሡ ናቸው:: በእርሱ በሁሉን አዋቂው፣ በፍፁም ጠቢቡ እንዲህ ተደንግጓል::**

**"በአምላክ መርከብ ውስጥ የሚኖሩ የባሃ ሕዝቦች ማናቸውም ሳይቀር እርስ በርሳቸው ስላላቸው ደረጃና ሁኔታ ደህና አድርገው ይተዋወቃሉ፣ በመቀራረብና በወዳጅነት ሰንሰለትም ይተሳሰራሉ። ሆኖም፣ እንዲህ ያለው ደረጃ በእምነታቸውና በምግባራቸው ላይ የተመሠረተ ነው። እነዚያ በአንድ ክፍልና ደረጃ የሚገኙት ስለእርስ በርሳቸው ችሎታ፣ ጠባይ፣ ስለአከናወኑት ሥራና ስለትቀዳጁት ክብር ሙሉ በሙሉ ይተዋወቃሉ። ሆኖም፣ እነዚያ ከዝቅተኛ ክፍል የሆኑት በደረጃ ከእነርሱ በላይ የሆኑትን ደረጃ፣ ወይም ብቃታቸውን ለመገመት ሙሉ በሙሉ መገንዘብ ያዳግታቸዋል። እያንዳንዱ ከጌታህ ድርሻውን ይቀበላል። ወደ ሁሉም ሉዓላዊ ጌታ፣ከሁሉ ይበልጥ ኃይል ወደተመላው፣ ወደ ዘለዓለም ይቅር ባዩ፣ ወደ ፍፁም ምህረትኛው አምላክ ነፍሱ እስክትበር ድረስ ፊቱን ወደ አምላክ አቅጣጫ ያዞረ፣ በፅናትም በፍቅሩ መንገድ የተራመድ ሰው የተባረከ ነው።"[28]**

1. በዚህ ዓለም ያወቅናቸውን ሰዎች በቀጣዩ ዓለም እናውቃቸዋለን?____________________።

2. በቀጣዩ ዓለም በነፍሳት መካከል ያለው ትስስር ምን ያህል ቅርብ ነው?______________
_______________________________________________________________
_______________________________________________________________

3. በቀጣዩ ዓለም በነፍሳት መካከል ያሉ ልዩነቶችና ማዕረጎች በምን ላይ የተመረኮዙ ናቸው?__
_______________________________________________________________

4. ከአምላክ ፀጋ የሚነፈግ ሰው ይኖራል?__________________________________________

## ምዕራፍ 22

**ባሃኦላህ እንዲህ ያሳስበናል፦**

**"አገልጋዮቼ ሆይ! በእነዚህ ቀናትና በዚህ በምድራዊ ደረጃ ከፍላጎቶቻችሁ ጋር ተቃራኒ የሆኑ ነገሮች በአምላክ ቢታዘዙና ቢገለፁ አትዘኑ፣የከፍተኛ ሐሴትና የመንግሥተ ሰማያዊ ደስታ ቀናት በዕርግጥ ተዘጋጅተውላችኋልና። የተቀደሱና በመንፈሳዊ ሁኔታ ክቡር የሆኑ ዓለማት ለዓይኖቻችሁ ይገለጣሉና። በዚህ ዓለምና በኋለኛው፣ ከጥቅሞቻቸው ለመሳተፍ፣ ከሐሴቶቻቸው ለመካፈል፣ ከሕይወት ሰጪው ፀጋቸውም ደርሻ ለማግኘት አስቀድሞ በእርሱ ተወስኖላችኋል። እያንዳንዳቸውን አንዳቸውም ሳይቀሩ ያለጥርጥር ትደርሱባቸዋላችሁ።"[29]**

1. ከሚከተሉት የትኞቹ እውነት እንደሆኑ ወስኑ:-

________ ነገሮች እንደምንፈልገው ካልሆኑ በሐዘን መዋጥ ይኖርብናል።

________ ጥሩም ሆነ ወይም መጥፎ፣ ሁሉም በአምላክ የታዘዙ ናቸው።

________ በከፍተኛ ሐሴት የተሞሉ የደስታ ቀናት ሁላችንንም ይጠብቁናል።

________ የተቀደሱና በመንፈሳዊ ሁኔታ ክቡር የሆኑ ዓለማት እንደምናይ ዕርግጠኞች ነን።

________ በዚህ ሕይወትና በወዲያኛው ሕይወት፣ የተቀደሱና በመንፈሳዊ ሁኔታ ክቡር የሆኑ ዓለማት ጥቅሞችን መካፈል የተወሰነልን ዕጣፈንታ ነው።

2. ከምንመኛቸው ተቃራኒ የሆኑ ነገሮች ሲያጋጥሙን በሐዘን መዋጥ የሌለብን ለምንድን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

3. በዚህ ምንባብ ውስጥ ባሃኦላህ ምን ቃል እየገባልን ነው?______________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

## ምዕራፍ 23

በዚህ ክፍል ውስጥ በሰው ሕይወት ትርጉም ላይ አሰላስላችኋል። ስለ ነፍስ ተፈጥሮ፣ በዚህ ዓለም ውስጥ የሕይወት ዓላማ፣ መንፈሳዊ ባሕርያትን የማሳደግ አስፈላጊነት፣ እንዲሁም ስለ ዘለዓለማዊ፣ ክቡርና በሐሴት ስለተሞላ ሕይወት የተሰጠንን ተስፋ በብዛት ተምራችኋል። በመጽሐፉ ሁለተኛ ክፍል፣ ስለ ሁለት እጥፍ ዓላማ ተነጋግረናል፦ የራሳችንን መንፈሳዊና አዕምሮአዊ ዕድገት ለመቀዳጀት እና ለኅብረተሰብ ለውጥ አስተዋፅኦ ለማበርከት። ስለ ነፍስ ዕድገት ባገኛችሁት ጥልቅ ዕይታ መሠረት፣ ወደዚያ ፅንሰሃሳብ ለመመልስና የዚህን ዓላማ ሁለቱንም ጎኖች ስለ መቀዳጀት አስፈላጊነት ለማሰብ ዕድሉ ቀርቦላችኋል። ከሥር ባሉት ጭብጦች ላይ በቡድናችሁ ከምታደርጉት ውይይት ያሰላሰላችሁባቸው ፅንሰሃሳቦች ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

1. መንፈሳዊ ባሕርያትን ማዳበር
2. የአምላክን ሕግጋት መታዘዝ
3. ለሰው ዘር ደህንነት አስተዋፅኦ ማበርከት
4. በአገልግሎት ጎዳና ላይ መገስገስ

## ማጣቀሻዎች


1. በኖቬምበር 10 1911 ከተሰጠ ንግግር፣ የፓሪስ ንግግሮች ውስጥ የታተመ:- በ 1911 በአብዱል—ባሃ የተሰጠ ንግግር (ዊልሜት:- ባሃኢ ኅትመት፣2006፣2016)፣ቁጥር 29. 12—13፣ ገጽ 109።

2. በኤፕሪል 1 1946 ሾጊ ኤፌንዲን በመወከል ከተጻፈ ደብዳቤ፣ በ 'ላይትስ ኦፍ ጋይዳንስ' ውስጥ የታተመ:- የባሃኢ ማጣቀሻ መዝገብ (ኒው ዴልሂ: ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1988፣ 2010)፣ ቁጥር 1820፣ ገጽ 537።

3. በጁላይ 28 2016 ዓለም ዓቀፍ ቤተ ፍትህን በመወከል ከተጻፈ ደብዳቤ።

4. አብዱል—ባሃ፣ 'መልስ በተሰጣቸው ጥያቄዎች' ውስጥ (ዊልሜት:- ባሃኢ ኅትመት፣ 2014፣ 2016)፣ ቁጥር 66. 3፣ ገጽ 352—53::

5. ዝኒ ከማሁ 38.5፣ ገጽ 220::

6. በኖቬምበር 10፣ 1911 ከተሰጠ ንግግር፣ የፓሪስ ንግግሮች ውስጥ የታተመ:- በ 1911 በአብዱል—ባሃ የተሰጠ ንግግር ቁጥር 28.16፣ ገጽ 104::

7. በዲሴምበር 31 1937 ሾጊ ኤፌንዲን በመወከል ከተጻፈ ደብዳቤ፣ በ 'ላይትስ ኦፍ ጋይዳንስ' ውስጥ የታተመ:- የባሃኢ ማጣቀሻ መዝገብ ቁጥር 680፣ ገጽ 204::

8. ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት' (ዊልሜት:- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 1983፣ 2017)፣ 82፣ አንቀጽ 8፣ ገጽ 183::

9. አብዱል—ባሃ፣ 'መልስ በተሰጣቸው ጥያቄዎች' ውስጥ ቁጥር 61. 1—2፣ ገጽ 334::

10. ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣ 80፣ አንቀጽ 2፣ ገጽ 174::

11. ዝኒ ከማሁ፣ 81፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 176::

12. ዝኒ ከማሁ፣ 165፣ አንቀጽ 1—3፣ ገጽ 391—92::

13. ባሃኦላህ፣ ኅቡዓተ ቃላት (ዊልሜት:- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2003፣ 2012)፣ አረብኛው ቁጥር 32፣ ገጽ 11::

14. በሜይ 5 1912 ከተሰጠ ንግግር፣ በዓለም ሰላም እወጃ ውስጥ የታተመ:- በ 1912 የዩናይትድ ስቴትስና ካናዳ ጉብኝቱ ወቅት በአብዱል—ባሃ የተደረጉ ንግግሮች (ዊልሜት:- ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2012)፣ ገጽ 315—16:: (ሕጋዊነት ያለው ትርጉም)

15. ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣ 5፣ አንቀጽ 4፣ ገጽ 8::

16. ዝኒ ከማሁ፣ 82፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 179—80::

17. ዝኒ ከማሁ፣ 153፣ አንቀጽ 6፣ ገጽ 370—71::

18. ዝኒ ከማሁ፣ 27፣ አንቀጽ 2፣ ገጽ 72—73::

19. ዝኒ ከማሁ፣ 27፣ አንቀጽ 3፣ ገጽ 73::

20. ዝኒ ከማሁ፣ 21፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 54—55::

21. ዝኒ ከማሁ፣ 81፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 177::

22. ዝኒ ከማሁ፣ 122፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 293—94::

23. ዝኒ ከማሁ፣ 82፣ አንቀጽ 7፣ ገጽ 182::

24. ዝኒ ከማሁ፣ 81፣ አንቀጽ 1፣ ገጽ 176—77::

25. ዝኒ ከማሁ፣ 125፣ አንቀጽ 3፣ ገጽ 300—1::

26. አብዱል—ባሃ፣ መልስ በተሰጣቸው ጥያቄዎች ውስጥ ቁጥር 62.3፣ ገጽ 340—41::

27. ከአብዱል—ባሃ ቅዱሳን ጽሑፎች የተመረጡ (ዊልሜት፡-ባሃኢ ኅትመት ትረስት፣ 2010፣ 2015)፣ ቁጥር 149.3—4፣ ገጽ 246—47::

28. ከባሃኦላህ ጽሑፎች ቅስማት፣ ቁጥር 86፣ አንቀጽ 1—2፣ ገጽ 192—93::

29. ዝኒ ከማሁ፣ ቁጥር 153፣ አንቀጽ 9፣ ገጽ 373::